# የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን

(Amharic)

**By**

**J.C.Choate**

**Published by:**

**World Evangelism Publications**

**Winona, Mississippi**

© Copyright, World Evangelism Publications

This printing - 5,000 copies - 2023 – **Amharic**

**InDesign Layout**: Shane Fisher

**Translated by**: Belay Kebede Areri
**WhatsApp number**:  0913611000.
**Email**: ddcoc321@yahoo.co.uk

**Websites**:
www.worldevangelismlibrary.org
www.gospelgazette.com
www.worldevangelism.org
www.worldevangelismmedia.com

**ማሳሰቢያ ይህ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ንብረት ነው፡፡ ይህ ትምህርት በነፃ የሚሰጥ ነው፡፡ በየትምህርቱ መጨረሻ ጥያቄ አለው፡፡ መልሶቻቹሁን በራሳቸው ነጭ ወረቀት ላይ ፅፋቸው መልስ መስጫውንና መጽሃፉን መልሱልን፡፡ ስትልኩ ለድሬዳዋ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፖስታ ሳጥን ቁጥር 1376 ድሬዳዋ፡፡ ብላቹሁ ላኩልን፡፡ ለበለጠ መረጃ 0913611000 ላይ መጠየቅ ይቻላል**

**Printed by**:
World Evangelism Publications
Winona, MS 38967

# ማውጫ


*ትምህርት አንድ ~
የቤተክርስቲያን ትርጉም.....................................4
*ትምህርት ሁለት~
የቤተክርስቲያን መምጣት.................................7
*ትምህርት ሶስት~
የቤተክርስቲያን መመስረት...............................11
*ትምህርት አራት ~
የቤተክርስቲያን ማንነት...................................15
*ትምህርት አምስት~
የቤተክርስቲያን ስም........................................19
*ትምህርት ስድስት~
የቤተክርስቲያን አደረጃጀት..............................23
*ትምህርት ሰባት~
ወደ ቤተክርስቲያን መግባት............................26
*ትምህርት ስምንት~
የቤተክርስቲያን አምልኮ...................................30
*ትምህርት ዘጠኝ~
የቤተክርስቲያን ሥራ.......................................33
*ትምህርት አሥር~
የቤተክርስቲያን አንድነት................................37
*ትምህርት አሥራ አንድ~
የቤተክርስቲያን እምነት...................................40
*ትምህርት አሥራ ሁለት~
የቤተክርስቲያን ታሪክ.......................................44
*ትምህርት አሥራ ሶስት~
የዛሬዋ ቤተክርስቲያን....................................48

## ትምህርት አንድ
## የቤትክርስቲያን ትርጉም

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሚናገር የሚከድ የለም፡፡ነገር ግን የትኛዋ ቤተክርስቲያን ናት? የማን ቤተክርስቲያን ናት?ምንድናት? የሚሉት እና ሌሎች ጥያቄዎችም ይነሳሉ። እነዚህም ለጊዜ ናቸው ይመለሳሉ። አሁን ቤተክርስቲያን ምንድን ናት? የሚለውን የምንመረምርበት ሲሆን የምንጀምረው ቤተክርስቲያን ልትሆን ከማትችላቸው ነገሮች እንጀምራለን፡፡በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጽው ቤተክርስቲያን ካቶሊክ፣ጴንጤ፣ፕሮተስታንት፣ኦርቶዶክስ አድቬንተስት ሞርሞን ወዘተ ልትሆን አትችልም፡፡

የሐይማኖት ድርጅት ሴክተሪያን ልትሆን አትችልም፡፡የፖለቲካ ድርጅት፣ማህበራዊ ድርጅት፣እድር፣የቁሳቁሳዊ ስብሰባ ቤትም ልትሆን አትችልም፡፡እሺ ቤተክርስቲያን ከዚህ በላይ የተጻፉትን መሆን ካልቻለች ምን ልትሆን ትችላለች? ብዙ ሰዎችቤተክርስቲያንን አልተረዷትም፡፡ ምክኒያቱም ምን እንደሆን አላወቁም። ውጤቱም የቤተክርስቲያንን ዓላማ አለማወቅ አለማወቅ ነው፡፡ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ስለ ቤተክርስቲያን ይናገራል፡፡

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ሲሆን ኤክሌሺያ ማለትም “የተጠሩት” ማለት ነው፡፡ስለዚህ ቤተክርስቲያን ከዓለም የተጠሩ ማለት ነው፡፡(ቆላስያስ 1፡13)የክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ፡፡(ቆሮንቶስ 12፡27) ክርስቶስን የታዘዙት ስብስብ። (ቆላስያስ 5፡8~9) እና የዳኑ እና ወደ ቤተክርስቲያንበጌታ የተጨመሩ ናቸው፡፡(ማርቆስ 16፡16,ሐዋርያት ስራ 2፡47)በሌላ አባባል ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ተከታይ ወይም ደቀመዛሙርት ነው፡፡

ቤተክርስትያን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው በሁለት መንገድ ነው። በመጀመሪያ በሁለንተናዊ መልኩ የተነገረ ነው። ክርስቶስም እንዲ ባለበት ጊዜ በአእምሮው ይዞት ነበር። “ እኔም እልሃለው አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም አለት ላይ ቤተክርስቲያን እሰራለው የገሃነም ደጆችም አይችሏትም፡፡” ( ማቴ 16፡18)

ስለ ቤተክርስቲያን ሁለንተናዊነት ብዙ ጥቅሶች ከመጽሃፍ ቅዱስ እናገኛለን። ስለዚህ በየትኛውም ቦታ ቤተክርስቲያን ባለችበት፣ቤተክርስቲያኑዋ በመጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ከሆነች ያቺ እየሱስ ቤተክርስቲያኔን እሰራለው ያላት ናት፡፡ሁለተኛው በአካባቢው ሁኔታ ወይም መንገድ ይሆናል። ለምሳሌ ጳውሎስ በሮም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን ሲጽፍ እና ስለ ብዙ ማህበራት ወይም አብያተ ክርስቲያናት ሲናገር እንዲህ አለ። “ የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችዋል” ( ሮሜ 16፡16)

ይህንን እንዲ ሃይምኖት ድርጅቶቸ ስለ ብዙ ቤተክርስቲያን እያለ አይደለም። ነገር ግን የጌታ ቤተክርስቲያን ሆና በተለያየ አካባቢ ስላሉት መናገሩ ነው። ለበለጠ ማብራሪያ በቆሮንቶስ,በኤፌሶን,በፊሊጲስዮስ ወዘተ ስላሉት ቤተክርስቲያን እንደሚናገርታስተውላለህ።(1ኛ ቆሮንቶስ 1፡2 ኤፌሶን 1፡1 ፊሊጲሲዮስ 1፡1 )። እነዚህ ነገሮች ብዙዎችን ግራ ያጋባሉ።ምክኒያቱም ስለ ቤተክርስቲያን የሚያስቡት በሃይማኖት ድርጅት ልምዳቸው ስለሆነ ነው። ነገር ግን ስለ ሃይማኖት ድርጅት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ አናገኝም።

ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ስለብዙ ማህበር ይናገራል። እያንዳንዱ ጉባኤ የጌታ ቤተክርስቲያን የሆነው በ ማህበረሰቡ ውስጥ ነው። ነገር ግን ሁሉም በአንድ ላይ የቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ ያቀፈ ነው። ይህንን ለማወቅ አንድ ሰው የሃይማኖት ድርጅትን ቸላ ብሎ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመሄድ ጌታ የሰጣትን ቤተክርስቲያን ሊያይ ማለትም የጌታን ቤተክርሲያን ሲያነብ እና ሲረዳ ነው።

የቤተክርስቲያንን ትርጉም የበለጠ ለመረዳት እንዲረዳን እንግዲያውስ መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን እንዴት እንደ ሳላት እንመልከት።

1.የክርስቶስ አካል፡~ እርሱ ራሱ የክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ነው። ራሱም የክርስቶስ ነው።(ኤፌሶን 5፡23) አንድ አካል ብቻ አለ።(ቆላስያስ 1፡18)

2.የእግዚአብሔር ቤት ለቅዱሳኑ መጽሐፍት ውስጥ ቤት የሚለው ቃል ቤተሰብን ይጠቁማል። ይሕም ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆኗን እንድንረዳ ያረገናል።በ1ኛ ጢሞቴዮስ 3፡15 ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቤት የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንደሆነ ይናገራል።እግዚአብሔር አባታችን ነው።እኛም ልጆቹ ነን(ገላ 3፡ 26~27,ኤፈኦን 1፡3)

3.የእግዚአብሔር መንግስት፡~መንግስት ንጉስን ያሳያል ስለዚህም ክርስቶስ ንጉስ ነው።(ራዕይ 17፡14) ንጉስ ለመሆን አሁን መንግስቱ መኖር አለበት እርሱም ይኖራል። ( የሐዋርያት ስራ 8፡12) እኛ ተባዢዎቹ ነን። ዓለም ግዛቷ አዲስ ኪዳንም ' ናቸው። ይህቺ ቤተክርስቲያን ናት። (ማቴ 16፡18~19)

4.የጌታ የወይን ግንድ ፡~ ክርስቶስ የወይን ግንድ ነው። እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ቅርንጫፎቹ ነን።(ዩሃንስ 15፡1~8) እዚህ ቦታ ያለው ሃሳብ በወይኑ ቦታ መስራት እና ለገታ ፍሬ ማርባት ነው።

ቤተክርስቲያን በዚህ መልኩ ትገልጻለች። እባክዎትን እነዚህን ጉዳዮች ከቅዱሳት መጸሃፍት አጥኑ። እና ለራስዎ ይመልከቱ። ቤተክርስቲያንን እግዚአብሔር እንድትመለከትዋት እንደ ስራ የምታዩት ከሆነ አስተሳሰብዎ ሁሉ ምናልባትም ህይወትዎም ይለወጣል።

## ጥያቄዎች

### እባክዎትን አዎን ወይም አይደለም ብለው ይመልሱ

1.መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስቲያን ይናገራል? ________________

2.ቤተክርስቲያን ማለት ካቶሊክ ነው? ________________

3.አብዛኞቻቸውሰዎችቤተክርስቲያንንተረድተዋል?______________

4.ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በ አንድ መንገድ ነው የተገለጸው? _______________

5.ክርስቶስ ቤተክርስቲያኔን እሰራለው ብሏል? ________________

6.የኤሽያ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ሰባት የተለያዩ ሃይማኖት ድርጅት ያመለክታሉ? _______________________

7.ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት? _______________

8.አንድ አካል አለ? _____________

9.ክርስቶስ የቤተክርስቲያን እራስ ነው? ______________

10.መንግስቱ ገና አልመጣም? ___________

እባክዎትን ትክክለኛ መልስ ስጡ

1.ቤተክርስቲያን ልትሆን የማትችለውን የተሰነውን ጥከስ?
_______________________________________________________________________
_____________

2.ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ምን ከሚባል የግሪክ ቃል የመጣ ነው?
_______________________________________________________________________
_____________

3.ቤተክርስቲያን ምንን ያቀፈቾ ናት?
_______________________________________________________________________
_____________

4.ሁለቱ ቤተክርስቲያን የተገለጸቾባቸው መንገድ ምንድናቸው?
_______________________________________________________________________
_____________

5.ማነው ቤተክርስቲያንን ይሰራል ያለው?
_______________________________________________________________________
_____________

6.ስንት ቤተክርስቲያን ነው የሚሰራው ?
_______________________________________________________________________
_____________

7.ሰባቱ የኤሽይዝ ቤተክርስቲያናት ምን ነበሩ?
_______________________________________________________________________
_____________

8.ስንት አካል ነበሩ?

______________________________________________________
____________
**9.የነገስታት ንጉስ ማን ነው?**

______________________________________________________
___________
**10.በወይን ግንድ ውስጥ እኛ ምን ማድረግ አለብን?**

______________________________________________________
___________

**እባክዎትን አብራሩ**

**1.ኤክሌሽያ፡~________________________________________**
________________________

**2.የክርስቶስ አካል፡~____________________________________**
_____________________

**3.የእግዚአብሔር ቤተሰብ፡~________________________________**
___________________

**4.የእግዚአብሔር መንግስት፡~______________________________**
___________________

**5.የጌታ የወይን ግንድ፡~__________________________________**
___________________

## ትምህርት ሁለት
## የቤተክርስቲያን አመጣጥ

**ቤተክርስቲያን ድንገት በአንድ ቀን የመጣ አይደለም፡፡በእቅድ፣በትንቢት፣በተሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት ተመሰረተች፡፡መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን በግልጽ ያሳያል፡፡**

**በመጀመሪያ፡~ ቤተክርስቲያን ከመመስረቷ በፊት ቀድሞውኑ በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ነበረች፡፡ጳውሎስ ይህንን ለኤፌሶን ቅዱሳን ሲያውጅ “በክርስቶስ ሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የበረከን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡፡አለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን፡፡በበጎ ፈቃድ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ በእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን፡፡በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የያፀጋው ክብር ይመስገን ዘንድ ይህን አደረገ፡፡”(ኤፌ 1፡3~6)**

**እባክዎትን ያስተውሉ ጳውሎስ እያለ ያለው እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት መምረጡን እየገለጸ ነው፡፡ይህም ማለት እግዚአብሔር ስለ ቤተክርስቲያን ያሰበው ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ነው፡፡በዚያን**

ጊዜ አሰበ።ይህም በእሱ አእምሮው የተቀረጸ መሆኑ ነው።እንግዲህ እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያው ያቀደውን የእሱን ሥራ ማቃለል ማንኳሰስ ምንኛ ሞኝነት ነው።

ሁለተኛው፡~ቤተክርስቲያን በቡ አጋጣሚዎች በትንቢት ተነግሮ ነበር።ነብዩ ኢሳያስ“በዘመኑም ፍጻሜ የእግዚአብሄር ቤት ተራራ በተራሮች ላይ ጸንቶ ይቆማል።በኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል።አሕዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ።ሕግ ከጺዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከእየሩሳሌም ይወጣልና።ብዙዎች አሕዛብ ሄደው ‘ኑ ውድ እግዚአብሄር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣእርሱምመንገዱንያስተምረናል።በጎዳናውምእንሄዳለን’ይላሉ በአህዛብም መካከል ይፈርዳል።በብዙ አህዛብም ላይ ይበይናል”(ኢሳያስ 2፡2~3)

ነብዩ እዩኤልም “ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል መንፈሴን በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለው።ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸሁም ትንቢት ይናገራሉ።ሽማግሌዎቻቸሁም ሕልምን ያልማሉ።ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ።ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባርያዎች ላይ መንፈስን አፈሳለሁ።”(እዩኤል 2፡28~29) ነብዩ ዳንኤልም “በእነዚያም ነገስታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግስት ያስነሳል።ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግስት ይሆናል።እነዚያንም መንግስታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች።ለዘላለምም ትቆማለች” አለ። (ዳንኤል 2፡44)

አሁን አንዳንድ መደምደሚያዎችን እናድርግ

1. መንግስቱ በመጨረሻ ዘመን ይመሰረታል።
2. ይህም በተራሮች ላይ ይቆማል።
3. አህዛብ ሁሉ ወደ እርሱ ይሄዳሉ።
4. እግዚአብሔር በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሱን ያፈሳል።
5. ሌሎቹን መንግስታት ይፈጫቸዋል ያጠፋቸዋል ለራሱ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይቆማል።

እነዚህ ከላይ የተባሉት ትንቢቶች የት ተፈጸሙ?

የሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 2 አንብብ።

ሶስተኛ፡~ቤተክርስቲያን ተስፋ የተገባላት ናት።ዮሐንስ ሲናገር “የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች” አለ።(ማቴ 3፡2)ይህ ማለት ተቃርቧል።በቅርብ ጊዜ ይመሰረታል ማለቱ ነው።ክርስቶስም “እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ።በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለው። የጀሃነም ደጆች አይችሏትም” ብሎ ተስፋ ሰጥቷል።(ማቴ 16፡18) በመቀጠልም “እውነት እላችኋለሁ በዚህ ከቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግስት በሃይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ” አላቸው።(ማርቆስ 9፡1)እንዲህም

አላቸው "ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል።በስሙም የአጥያት ንሰሓና የአጥያት ስርየት ከእዬሩሳሌም ጀምሮ በአህዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል እናንተም ለዚህምስክሮቼናችሁእነሆአባቴየሰጠውንተስፋእኔእልክላችዋለሁ። እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በእየሩሳሌም ከተማ ቆዩ አላቸው። "(ሉቃስ 24፡46፡49) እንግዲህ እንዚህን እውነታዎቹ እንመልከት።

1. መንግስት ተቃርባለች።

2. ክርስቶስ እንደሚገነባት ቃል ገብቷል።

3. ከክርስቶስጋርየነበሩመንግስቱእስከሚመሰረትድረስበሕይወት እንደሚኖሩ ተነግሯል።

4. በሐይል እንደምትመጣ ተናግሯል።

5.ንሠሀና የሀጥያት ስርየት በስሙ በአሕዛብ ሁሉ ዘንድ እንደሚሰበክ ተናግሯል።

6. በእየሩሳሌም እንደሚጀመር ተናግሯል።

7.ሐዋርያቶች እየሩሳሌም እያሉ ከላይ ሐይል መጥቶ እንደሚወርድባቸው ተናግሯል።

በመጨረሻ ወደ ቤተክርስቲያን ምስረታ ስንመጣና ይህሁሉ ሲፈጸም ስለምታዩ እባክዎትን እነዚህን ሁሉ ነጥቦች ያስታውሱ።

አሁን ወደ ሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይመለሱና ምዕራፍ ሁለት ደጋግማችሁ በጥንቃቄ ያንብቡ።

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ቤተክርስቲያን የተመሰረተችሁ በዚህ ጊዜ እንደሆነ ያምናሉ።ከዚህም በላይ ቦታው እየሩሳሌም ነበር።ዘመኑም የመጨረሻ ዘመን ነበር።የሮማዊያን ነገስታት ዘመን ነበር።ቃል የተገባው ሀይልም መጣ።ንሰሃና የሀጥያት ስርየት በስሙ ለአህዛብ ሁሉ ተሰበከ።ቤተክርስቲያንም ከዚያን ቀን ጀምሮ ኖረች።ስለዚህ በእግዚአብሔር አዕምሮ ውስጥ የነበረች ቤተክርስቲያን ተመሰረተች።ስለእርሷየተነገሩትንቢቶችሁሉተፈጽመዋል።ስለእርስዋ የተነገሩ ተስፋዎች ሁሉ ተጠብቀዋል።

## ጥያቄዎች

### ትክክለኛውን መልስ ይመልሱ

1. በመጀመሪያ ቤተክርስቲያን የት ነበረች?___________________
___________

2. እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን የመረጠው መቼ ነው?_______
________________________

3. ስለ መንግስት መምጣት የተናገሩትን ሶስቱን ነብያት ስም ግለጽ___________________________

4. መንግስቱ ለምን ያህልጊዜ ይቆማል?________________________
________
5. ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ ያለው ማነው?______________________________
6. የማንን ቤተክርስቲያን ለመስራት ነው ቃል የገባው?________
_________________________
7. ስንት ቤተክርስቲያነ እመሰርታለሁ አለ?________________________________
8. መንግስቱ የመጣው በምንድ ነው?_______________________________________
9. በእየሩሳለም የተሰበከው ምንድ ነው?____________________________________
10. ስለቤተክርስቲያን ምስረታ የቱ ጋር ነው የምናነበው?__________________________________

እውነት ወይም ሐሰት ብለህ መልስ

1. ቤተክርስቲያን ታቀዷቸ ተተነበየቸ ቃል ተገባላት ተመሰረተቸ፡፡_____________
2. ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ነበረቸ፡፡________________
3. ዮሐንስ የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለቸ አለ፡፡_____________
4. የእግዚአብሄር መንግስት በሀይል መጣቸ፡፡_____________
5. ንሰሀና የሀጥያት ስርየት ለአህዛብ ሁሉ በስሙ ይሰብካል፡፡_____________
6. ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ስለቤተክርስቲያን ምስረታ ይነግራል፡፡______________
7. ቤተክርስቲያን የተጀመረቸው በእየሩሳሌም ነው፡፡_______________
8. ይህ የሆነው በሮማዊያን ነገስታት ዘመን ነው፡፡_______________
9. የመጨረሻ ዘመን ተጀምሯል፡፡_____________
10. የተነገሩት ትንቢቶቸና ተስፋዎቸ ተፈጽመዋል ተጠብቀዋል፡፡_______________

ባዶ ቦታ ሙላ

1. “_______________________________________________________

__ በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።

2. ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል _______________________
________________________________

3. የሰማይ አምላክ ለዘላለም _____________________ ያስነሳል።

4. ____________________እሰራለሁ።

5. ንሰሐ እና የሐጥያት ስርየት __________________።

## ትምህርት ሶስት
## የቤተክርስቲያን መመስረት

በቀደመው ትምህርታችን ከኢሳያስ 2፡~2~3፤ ኢዩኤል 2፡28~29፤ ዳንኤል 2፡44 ስለ እግዚአብሔር መንግስት ስለገታ ቤተክርስቲያን አይተናል። በነዝህም ውስጥ በመጨረሻ ዘመን እንደምትመሰረት በታውም ኢየሩሳሌም እንድሆነ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ወደዚያ እንደሚሄዱ አህዛብ ሁሉ ወደዚያ እንደሚሄዱ ለዘላለምም እንደሚቆም አይተናል።ክርስቶስ በማቴዎስ 16፡18 እና በሉቃስ 24፡ 45~49 ላይ ቤተክርስቲያኑን እንደሚሰራ በሃይል እንደምትመሰረት ንሰሓ እና የሓጥያት ስርዬት በስሙ በአህዛብ ሁሉ ዘንድ እንደሚሰበክ ተናግሮአል። አሁንም ወደ ሓዋርያት ስራ 2 በመመለስ በዚህ ምዒራፍ ብቻ ትንቢቶቹ እንዴተፈጸሙና የተሰጡት የተስፋ ቃሎችም እንደተጠበቁ ተረድተናል።

ወደዚሁ ሀዋሪያት ሥራ 2 ስንመለስ ሐዋሪያቶች በዚህ በክስተቱ ሰአት በእየሩሳሌም ነበሩ። “በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ንፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትን ቢት ሞላው።እንደእሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው።በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈሱም ይናገሩ ዘንድ እንዲሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በእየሩሳሌም ይኖሩ ነበር። ይህም ድምጽ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ።እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ።”(ሐዋርያት ሥራ 2፡1~6)ይህ ትንግርት በመቀጠል ሁሉንም አሕዛብ ወክለው በዚያ ስለተገኙት በመግለጽ ይቀጥላል። “ሁሉም ተገረሙናአመንትተው እርሥ በእርሣቸው ፡~እንጃ ይህ ምን ይሆን? አሉ።ሌሎች ግን እያፌዙባቸው ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ።ድምጹንም ከፍ አድርጎ

እንዲህ ሲል ተናገራቸው፡-አይሁድ በእየሩሳሌም የምትኖሩ ሁላችሁ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን።ቃሎቼንም አድምጡ።ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም።ከቀኑ ሶስተኛ ሰዓት ነውና ነገር ግን ይህ በነብዩ እዩኤል የተባለው ነው።እግዚአብሔር ይላል፡- “በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል።ስጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለው።ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ።ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ ሽማግሌዎቻችሁም ህልም ያልማሉ።የጌታን ስም የሚጣራም ሁሉ ይድናል”(የሐዋርያት ሥራ 2፡ 12-17,21)የሆነው ሁሉ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጽሜ መሆናቸውን ካሳየ በኋላ ጴጥሮስ ስብከትን ጀመረ።እግዚአብሔር በመካከላቸው ባደረገው ተአምራትና ድንቅ በምልክቶችም እየሱስ በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ ሰው እንደነበረ ያሳያል።በመቀጠል ክርስቶስ እንዴት እንደተወሰደ እና ወደ ሸንጎ እንደተሰጠ እና በክፉ እጆች እንደተሰቀለ እንደሞተ ይተርካል።ከዚያም እግዚአብሔር ሞትን ሥቃይን አጥፍቶ እንዳነሳው ገለጸ ይህንንም አድማጮቹን ለማሳመን እንደኖረ እንደሞተ እንደተቀበረ እና እንደተናነሳ ከዚያም በእግዚአብሔር ቀኝ ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ወደ ሰማይ እንዳረገ ዳዊትን ጠቅሶታል።በመቀጠልም እንዲህ ይላል “ይህንን እየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን።ስለዚህ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትን እና የምትሰሙትን አፈሰሰው።ዳዊት ወደ ሰማያት አልወጣምና ነግር ግን እርሱ ጌታዬን፡-ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።አለ እንገዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን እየሱን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በርግጥ ይወቅ።ይህንም በሰው ጊዜ ልባቸው ተነካ። ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት፡- ‘ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?’ አሏቸው።ጵጥሮስም፡- ‘ንሰሃ ግቡ ሐጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በእየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ የተስፋው ቃል ለእናንተ እና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችን ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና’ አላቸው።በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና፡- ‘ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ’ ብሎ መከራቸው። ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሶስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ።እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በህዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው ጌታም የሚድኑትን ዐለት ዐለት በእነሱ ላይ ይጨምር ነበር።” (የሐዋርያት ሥራ 2፡32-41,47)

ከላይ የተገለጹት የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍል የጌታ ቤተክርስቲያን ተመሰረተች።ይህ ሁሉ የሆነው በእየሩሳሌም እንደሆን ታስተውላለህ።የመንፈስ ቅዱስ ሃይል በሀዋርያት ላይ ፈሰሰ።የሆነውም

ለብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ ነው።ጴጥሮስ ይህንን ለይቶ ትናግሯል። እንዲህ ሲል ፦ "ይህ በነብዩ እዩኤል የተባለው ነው" አለ።(ሐዋርያት ሥራ 2፡16)ስለዚህም ጉዳይ እርግጠኛነት ጥርጥር የለውም።ከዚህም በላይ ነብያት የተናገሩት ነገር በመጨረሻው ዘመን ይሆናል።ጴጥሮስም "ነብዩ እንደተናገረው ሆኗል" ካለ በኋላ ቤተክርስቲያን በመጨረሻው ዘመን ተመሰረተች። በዚያን ቀን ንሰሃና የሃጥያት ሥርየት ሲሰበክ ሁሉም አህዛብ ተገኝተው ነበር። 3000 ያህሉ ደግሞ ታዛዦች ሆነው ድነዋል።እናም ወደ ቤተክርስቲያን ተጨመሩ። ስለዚህም ክርስቶስ በ33ዓ.ም በእየሩሳሌም ቤተክርስቲያንን መስርቶ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትኖራለች።

## ጥያቄዎች

## ማን እንደተናገረ ግለጽ

1. ማነው ቤተክርስቲያንን እሰራለው ያለው?________________ ____________________
2. ማነው "እግዚአብሔር ይላል በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ" ያለው ማነው?____ __________________________________________
3. "ጌታ ጌታዬን በቀኜ ተቀመጥ" ያለው ማነው?____________ _____________________
4. ማነው "ንሰህ ግቡ ሐጥያታቸሁን ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳቸሁ በእየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" ያለው ማነው?____ _____________________________________
5. ማነው "ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ" ያለው ማነው?_____ ____________________________________

## ትንቢቶቹን ተናገር

1. መቼ ነው የጌታ መንግስት የተመሰረ ተው?_________________________________
2. በየትኛው ከተማ ነው የተመሰረ ተው?_______________________________________
3. ስንት ሰዎች ናቸው ወደዚያ የሄዱት?_____________________ ______________________
4. ከምን ጋር ይመጣል?____________________________________ _____
5. ለምን ያህል ጊዜ ይቆማል?______________________________ ______________

## የተሰጡ ተስፋዎቸን ግለጽ

1. ቤተክርስቲያንን ማን ይሰራል?_______________________________
2. ከምን ጋር ይመጣል?_______________________________
3. ምን ይሰበ ካል?_______________________________
4. በስንት ህዝብ መሃል ይሰበ ካል?_______________________________
5. እነዚህ ሁሉ በማን ስም ይሰበካሉ?_______________________________

## እነዚህን ጥያቄዎቸ ከሐዋርያት ሥራ 2 መልሱ

1. መንፈስን የተቀበሉ እነማን ናቸው?_______________________________
2. ምልክቱ ምንድን ነው?_______________________________
3. ጴጥሮስ ሰዎቹን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዴት አናሳመና ቸው?_______________________________
4. እነሱ ምን አይነት ጥያቄ ጠየቁ?_______________________________
5. የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያን የሚጨምራቸው ማነው?_______________________________

## ከዚህ በታቸ ያሉትን አብራራ

1. ቤተክርስቲ ያን_______________________________
2. ትንቢት_______________________________
3. ጴንጤቆ ስጤ_______________________________
4. ንሰሃ_______________________________
5. ጥምቀት_______________________________

## ትምህርት አራት
## የቤተክርስቲያን ምንነት

ለረጅም ጊዜ የጠፉ ጓደኛ ለማግኘት እንዴት ታቅዳለህ?በቀላሉ ሁሉንም የመታወቂያ ምልክቶቹን ጸበስባለህ እናም ከዚያ ፍለጋውን ትጀምራለህ፡፡ከእያንዳንዱ የመታወቂያ ምልክት ጋር የሚዛመድ ነገር ግለሰቡን ካገኘህ በኋላ ብቻ ነው እየፈለክ እንደነበር የምትቀበለው፡፡በተመሳሳይም በዓለም ላይ ብዙ ቤተክርስቲያኖች አሉ፡፡ትክክለኛውና ኦርጅናሉ የትኛው እንደሆነ እንዴት ማወቅ ይቻላል?የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የትኛው እንደሆነች እንዴት ማወቅ ይቻላል?እንግዲህ ሁሉንም የመታወቂያ ምልክቶች ወስደህ ከተለያዩ ቤተክርስቲያኖች ጋር ማወዳደር አለብህ፡፡ከእያንዳንዱ የመታወቂያ ምልክት ጋር የሚስማማውን ካገኘህ በኋላ ብቻ ትክክለኛውን ማግኘትህን እርግጠኛ መሆን ትችላለህ፡፡ግን የመታወቂያ ምልክቶቹ ምንድናቸው?የትስ ይገኛሉ?ለነዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መልሶች አሉት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ለእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን መታወቂያ ምልክት ሰጥቷል፡፡ስለዚህ እነዚያ ምልክቶች ምን እንደሆኑ ለማየት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ፡~

1. ቤተክርስቲያንን ክርስቶስ መስርቷል፡~"እኔም እልሃለው አንተ ጴጥሮስ ነህ በዝሂችም ዕለት ላይ ቤተክርሥቲያኔን እሰራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም" (ማቴዎስ 16፡18)፡፡

2. መነሻው ወይም መጀመሪያው በእየሩሳሌም ነበር፡~ ይህም በሉቃስ 24፡45~49፤በሐዋርያት *ሥራ* 2፡5 ውስጥ ይታያል፡፡

3. ቤተክርስቲያን የተወለደችው በ33ዓ.ም ነበር፡፡ይህ ደግሞ በሐዋርያት *ሥራ* 2 ላይ ቤተክርስቲያን በጴንጤቆስጤ ቀን መመስረቷ ይገልጻል፡፡

4. ቤተክርስቲያን የክርስቶስን ስም ለብሳለችለብዙ አብያተ ክርስቲያናት ጳውሎስ ሲናገር "የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላችዋል" (ሮሜ 16፡16) ቀጥሎም ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲናገር "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፡፡እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ፡፡" (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡27)፡፡ነገር ግን አካል ምንድነው?አካል ማለት ቤተክርስቲያን ናት፡፡(ኤፌሶን 1፡22,23)

5. አባላቶቿክርስቲያንየታባሉናቸው፡፡"በቤተክርስቲያንምአንድ አመት ሙሉ ተሰበሰቡ ብዙ ህዝብንም አስተማሩ፡፡ደቀመዛሙርትም መጀመሩያ አንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ፡፡(የሐዋርያት *ሥራ* 11፡26) "አግሪጳም ጳውሎስን ፡~በጥቂት ክርስቲያን ልታረገኝ ትወዳለህ" አለው፡፡(ሐዋርያት ስራ 26፡28) "ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህስም እግዚአብሄርን ያመስግን" (1ኛ ጴጥሮስ 4፡16)

በመጨረሻም ይህንን አስታውስ "መዳንም በኬካ በማንም የለም እንድንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።" ( የሐዋርያት ስራ 4:12)

6. የቤተክርስቲያን ራስ ክርስቶስ ብቻ ነው።"እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው። እርሱም ከሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው።" (ቆላስያስ 1:18)

7. እሱ አንድ ነው። "በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካክልና አንድ መንፈስ አለ።" (ኤፌሶን 4:4)ግን አካል ምንድነው? እሱም ቤተክርስቲያን ነው። (ቆላስያስ 1:18) ስለዚህ አንድ አካል ካለና ያ አካል ቤተክርስቲያን ከሆነ ያቺ ቤተክርስቲያን አለች።

8. ወደዚህ ቤተክርስቲያን ለመግባት ውሎች ወይም መስፈርቶች አሉ።እነሱም የሚያጠቃልሉት እምነት (ዕብራውያን 11፡ 6) ንሠሐ መግባት (የሐዋርያት *ሥራ* 17:30) መመስከር (ሮሜ 10፡ 9,10) እና ጥምቀት ናቸው (ማርቆስ 16:16) ሰው አንዴ ከዳነ ወደ ቤተክርስቲያን ይጨመራል(ሐዋርያት *ሥራ* 2:47) እንዲሁም ሮሜ 6፡ 3,4) (ገላትያ 3:26,27) እና (ቆሮንቶስ 12:13) የሚያስተምሩትን ሰው በክርስቶስ እና በቤተክርስቲያኑ መጠመቁን ሲሆን ወንጌልን የሚታዘዝ አንድ ሰው ደግሞ በመወለድ ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንደ ሚገባ ነው።(ዩሃንስ 3:3~5)

9. የቤተክርስቲያኒቷ አምላክ ልዩ ነው፡~ክርስቲያኖች ጌታን ለማምለክ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ይሰበሰባሉ (ሐዋርያት *ሥራ* 20:7) በዚህ አምልኮ ይዘምራሉ።(ኤፌሶን 5:19)ይጸልያሉ።(ሐዋርያት *ሥራ* 2፡ 42)መጽሐፍ ቅዱስን ይማማራሉ።(2ኛ ጢሞቴዮስ 2:15)የጌታ እራትን ይካፈላሉ።(1ኛ ቆሮንቶስ 11) ከሚያገኙት ላይ ይሰጣሉ።(1ኛ ቆሮንቶስ 16:2)

10. የቤተክርስቲያኒቷ ዶክትሪን(ትምህርት)በፊጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው።ይህም መጽሐፉን ሳትጨምር ሳትቀንስ ሌላም ሳትተካ እንዳለ ትቀበላለጭ(ዮሀንስ ራዕይ 22:18~19,ገላትያ 1፡ 6~11) መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን የምታምንባት አንድ እና አንድ ብቻ ነው።ተጨማሪ መጽሐፍትም ሆነ እምነት በጌታ ቤተክርስቲያን ተቀባይነት የለውም።

11. የቤተክርስቱያን አደረጃጀት እንደ እግዚአብሔር እቅድ መሆን አለበት።ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው።(ኤፌሶን 5:23) እያንዳንዱ ማህበር የየራሳቸው የቤተክርስቲያን ሽማድሌዎች እና ዲያቆናት አሏት (1ኛ ጢሞትዮስ 3,ቲቶ 1) የጌታ ቤተክርስቲያን በዚህ ምድር ራስ ወይም ጠቅላይ አዛዥ ወይም ሐገር አቀፍ ወይም አለም አቀፍ ሰው ሰራሽ አደረጃጀት የላትም።

12. የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ሶስት ነው።*ሥራ*ዋ ወንጌልን መስበክ

(ማርቆስ 16፡15~16)ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን መደገፍ መርዳት (ገላትያ 6,ያዕቆብ 2)አካላትን ማነጽ (ዕብራውያን 3፡12~14)

13. እያንዳንዱ ክርስቲያን በታማኝነት የክርስቲያን ሕይወት እንዲኖር ነው፡፡በአለም ያለውን አንወድም (1ኛ ዮሐንስ 2፡15,ያዕቆብ 4፡4)ነገር ግን የመንፈስን ፍሬ እናፈራለን፡፡(ገላትያ 5፡22~23)በዚህ የጸና የሕይወት አክሊል ይቀበልቅልና፡፡(ዮሐ ራዕይ 2፡10)

እንግዲህ ስለ ቤተክርስቲያን መለያ ምልክቶች የተወሰኑት ናቸው፡፡እነዚህምየተገኙት ከመጽሐፍቅዱስ ነው፡፡እንግዲህ አንባቢው እነዚህ ውሰድ እራስህን ጠይቅ “ቤተክርስቲያኔን ማነው የሰራት?” “በክርስቶስ ወይስ በሌላ ሰው ተመሰረተች?”ቀጥልና እራስህን ጠይቅ “ቤተክርስቲያኔ የት ነው የተመሰረተችው?” በመጀመሪያ የተጀመረችው በእየሩሳሌም ነው ወይስ በሌላ ሃገር ወይም ቦታ?” ቀጥልና“መቼ ነው የተመሰረተችው?”ከ33ዓ.ም በኋላ ከሆን እሷ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ልትሆን አትችልም፡፡በመጨረሻም ጠይቅ “ቤተክርስቲያኔ የለበሰችው የማንን ስም ነው?”ሌላም መቀጠል ትችላለህ፡፡ነገር ግን ለጊዜው እነዚህ ቤተክርስቲያንህ የክርስቶስ ወይም የሌላ ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳህል፡፡ያንተን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም አብያተክርስቲያናት ከነዚህ መለያ ምልክቶች ጋር በማስተያየት የጌታ ይሁን የሰው መለየት ትችላለህ፡፡እርግጠኛ ነኝ በታማኝነት የምትመለከት ከሆነ በመካከላችሁ ያሉትን ልዩነቶች በቀላሉ መለየት ትችላለህ፡፡

አንተ ያለህበት ቤተክርስትያን ከዚህ ካነበብከው የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ጋር የሚለያይ ከሆነ ያንን እንድትተወውና መጽሐፍ ቅዱስን እንድታጠና እውነትን እንድታውቅ እንድትታዘዝ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ውደ አነበብከው የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቃል ወደ ተረዳኸው ቤተክርስቲያን እንድትጨመር አበረታታሃለው ይህም በትክክል ደህንነት ወደሚገኝበት የእግዚአብሔር መንግስት መቀላቀል ይሆናል፡፡

## ጥያቄዎች

## ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ለብዙ ጊዜ የተለየህ ጓደኛህን እንዴት ትፈልገዋለህ? ______
_______________________________________________________________
____________________________________________
2. በአለማችን ዛሬ ብዙ ቤተክርስቲያኖች አሉ? ____________
_______________________________________________________________
_____________________________________
3. አንድ ሰው ትክክለኛውን እንዴት ማወቅ ይችላል? ________

________________________________________________________________
____________________________________________
4. የመለያ ምልክቶች የት ነው የሚገኙት? __________________
________________________________________________________________
__________________________________
5. ቤተክርስቲያን የመሰረታት ማነው? ______________________
________________________________________________________________
________________________________
6. የተጀመረው በየት ከተማ ነው?________________________
7. መቼ ነው የተመሰረተችው?____________________________
8. ስሟን ጥቀሱ?______________________
9. አባላቶቿ ምን ተብለው ይጠራሉ?_______________________
10. አካል ምንድነው?__________________________
11. የቤተክርስቴያን ራስ ማነው?_______________________
12. ስንት ቤተክርስቲያኖች አሉ?________________________
13. ወደ ቤተክርስቲያን መግቢያ ውል ተናገር?________________
______________________________
14. ወደ ቤተክርስቲያን እንዴት ይጨመራል?________________
15. የአምልኮ ተግባራትን ግለጽ፡፡___________________________
______________________________________________________
16. የቤተክርስቲያን ዶክትሪን ምንድ
ነው?___________________________________
17. እያንዳንዱ ማህበር ሊኖሩት የሚገባቸውን ተናገር?_________
__________________________________
18. ሶስቱን የቤተክርስቲያን ተልዕኮዎችን ግለጽ?_____________
_______________________
19. ክርስቲያን ምን አይነት ህይወት ሊኖር ይገባ
ዋል?________________________________
20. የህይወት አክሊልን የሚቀበል ማነው?____________________
______________
21. ሰው ከሆነ የጀመረው የጌታ ቤትክርስቲያን መሆን ይችላል?_
__________________________________
22. በእያሩሳሌም ካልተመሰረተች የጌታ ቤተክርስቲያን ልትሆን
ትችላለች? ___________________________________________________
23. ከ33ዓ.ም በኋላ የተጀመረች ቤተክርስቲያን የጌታ ልትሆን
ትችላለች?____________________________________________
24. የክርስቶስን ስም ካልለበሰች የጌታ ቤተክርስቲያን መባል ትቸ
ላለች?_____________________________________________

25. ከጳንከ በኋላ ክርስቶስ በየትኛው ቤተክርስቲያን ይጨምር ሃል?________________________________________________

## ትምህርት አምስት
## የቤተክርስቲየን ስም

ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን ካለባት የቅዱሳት መጽሕፍ ስምሊኖራት ይገባል።ይሁን እንጂ ብዙ ሰው ሰራሽ ስሞችና ማድረግ ያለባቸው ብዙ ሰው ሰራሽ አብያተ ክርስቲያናት አሉ።እነዚህ እንዴት ሊሆኑ ቻሉ?ከነዚህ ስሞች አንዳንዶቹ የተሰጡት መስራቾቻቸውን ለማክበር ነው።እንደ “ሉተራን”ያሉ።አንዳንዶቹ እንደ ጥምቀት ወይም የጌታን ሥራ የመስራት ዘዴ ያሉ አስተምህሮችን ከፍ ያደርጋሉ።አንዳንዶቹ እንደ ጴንጤቆስጤ ወይም የሰንበት ቀንም ያከብራሉ።ሌሎቹ ደግሞ ለቤተክርስቲያኒቱም የሊቃነ መናብርት ሥራ መሰረት በማድረግ በመንድስት መልክ ላይ ያተኩራሉ።ነገር ግን እነዚህ ሁሉ እና ሌሎች ሊጠቀሱ የሚችሉትን ክብር፣ምስጋና፣እና ለክርስቶስ ወሰዱና ለሰዎች ሰጡ።

ሰው ሰራሽ ስሞች እና ማእረጎች በብዙ ምክንያት ስህተት ናቸው። በመጀመሪያ መከፋፈልን ያመጣሉ። ሰዎችን ይለያያሉ። እግዚሃብሄር መከፋፈልን ባልፈለገበት ቦታ እነሱ ግን ይለያያሉ። በዮሃንስ ወንገል 17 ላይ ተመዝግቦ የሚገኝን የክርስቶስን ጸሎት ይቃወማሉ። ሁላችንም አንድ እንድንሆን ጸልዮ ነበርና። ሁለተኛ በቅዱሳት መጽሃፍት መከፋፈል የተወገዘ ነዉ። በ 1 ቆሮንቶስ 1፡10~17 ላይ ሓዋሪያው ጳውሎስ የሰዎችን ስም የመልበስ ስህተትን ለወንድሞች አሳይቶአል ስለዚህ በፓርቲ እና በቡድን መከፋፈልን አውግዞአል። ሶስትኛ የሰዎች ስም በጌታ ስም ተተካ ሆኖም ኝ በመጽሃፍ ስለክርስቶስ ስም የምናነበው “መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና” (ሓዋሪያ ስራ 4፡12)። አራተኛ ሰው ሰራሽ ስሞች አሳሳች ግራ የሚያጋቡና በማያምኑት መካከል የተሳሳተ ግንዛቤ ይፈጥራሉ። አለማመንን ያስከትላሉ። አምስተኛ ስማቸውን የለበሱትን ሁሉና በነርሱ ምክንያት ከክርስቶስ የተመለሱትን ሁሉ እንዲጠፉ ያደርጋሉ። በነዚህ ምክንያቶች የተሳሳቱና ኃጥያተኞች ናቸው።

ክርስቶስ ቤትክርስቲያንን እንድሚሰራ ተስፋ ሰጥቶአል (ማቴዎስ 16~18) ቤተክርስቲያንም በደሙ እንድምትዋጅ ተነግሮአል (ሓዋሪያት ስራ 20፡28) አዳኝ እሱ ብቻ ነው (ኤፌሶን 5፡23)፣ የቤተክርስቲያን ራስ ክርስቶስ ነው (ቆላስያስ 1፡18) ስለዚህ የክርስቶስን ስም መልበስ መስራቹን ማክበር ራስ የሆናትን ያዳናትን ብቻ ማክበር እንዳለብን

የታወቀ ነው። ሓዋሪያው ጳውሎስ በሮም ሆኖ በአከባቢ ላሉት ሲጽፍ “የክርስቶስ አብያትክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል” አላቸው(ሮሜ 16፡16)።እንዲዚሁም ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲናገር “እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ” ብሎአቸዋል (1 ኛ ቆሮንቶስ 12፡27)።እንግዲህ አካል ከሆነ ያቺ አካል ቤተክርስቲያን ናት (ኤፌሶን 1፡22~23) ስለዚህ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው። እንዲዚሁም የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ተብሎአል (1 ቆሮንቶስ 1፡2፤ ሓዋሪያት ሥራ 20፡28)፤ የእግዚአብሄር መንግስት (1 ቆሮንቶስ 6፡9)፤ የክርስቶስ መንግስት (ኤፌሶን 5፡ 5)፤ የፍቅሩ ልጅ መንግስት ( ቆላስያስ 1፡13)፤ የጌታችን መንግስት ( 2ኛ ጴጥሮስ 1፡11) ቤትክርስትያን (ሓዋሪያት ሥራ 12፡1)፤ የህያው እግዚአብሄር ቤተክርስትያን ( 1 ጢሞቴዎስ 3፡15)፤ የበኩራት ማህበር (ዕብራዊያን 12፡23) ወዘተ ናቸው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በማንም ስትጠራ ወይም ምንም ዓይነት በማዕረግ ስም ስትጠራ አናነብም። እናም ቤትክርስቲያን የእግዚአብሄር የክርስቶስም ብቻ ናት ። ከላይ የተጠቀሱት መጽሃፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችም የሚነግሩን ክርስቶስ የመሰረታት መሆኑን ነው። ቤትክርስቲያን የክርስቶስ ካልሆነች የማን ልትሆን ትችላለች? በተጨማሪም በነዚህ ሁሉ ስሞች እና ገላጭ ማዕረጎች አንድ ሰው ከቅዱሳት መጽሃፍት በመራቅ ለጌታ ቤትክርስቲያን ሌላ ስያሜ መምረጥ እውነትን መካድ ይሆናል። ነገር ግን መጽሃፍ ቅዱስ ጋር እንቆይና ቤተክርስቲያንን መጽሃፍ ቅዱስ በሚጠራው ስንጠራት ያኔ ትክክል እንሆናለን።

እንዲዚሁም የቤተክርስቲያን አባላት መጠሪያን በተመለከተ ቅዱሳን መጽሃፍት በግልጥ ያሳያል። ለመጀመሪያ ጊዜ ነቢዩ ኢሳያስ አምላክ ለህዝቡ አዲስ ስም እንደሚሰጣቸው ተናግሮአል (ኢሳያስ 62፡ 2) ይህንን ነገር በነጳውሎስ የተገለጸው ከብዙ ዓመታት ቦኃላ ነው። (ሓዋሪያት ሥራ 9፡15) ነገር ግን አህዛብ እግዚአብሄርን የመታዘዝ ዕድል እስኪያገኙ ድረስ አልተገለጸም ነበር። ደቀመዛሙርት መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን በተባሉ ጊዜ ያትንቢት ተፈጸመ(ሓዋርያት ሥራ 11፡ 26)ቦኃላም ጳውሎስ ለንጉስ አግሪጳ በሰበከ ጊዜ ንጉስ አግሪጳ የተናገረው “በጥቂቱ ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ” አለው (ሓዋርያት ሥራ 26፡ 28)በመጨረሻም ጴጥሮስ የተናገረውን ስናነብ “ክርስቲያን እንደሚሆን ኝ መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሄርን ያመስን እንጂ አይፈር” ይላል። (1 ኛ ጴጥሮስ 4፡16)።ከዚህም የተነሳ በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ተከታይ አማኞች ወንጌልን የታዘዙት እና የቤተክርስቲያን አባል የሆኑት መጠሪያ ስማቸው ክርስቲያን እና ክርስቲያን ብቻ ናቸው። ጌታ አሁን በዚህ ዘመንም በዚሁ ስም ብቻ እንድንጠራ ይፈልጋል ምክንያቱም የተጻፈ ነውና። ከዚህ በተረፈ ከቤተክርስቲያን እና ክርሥቲያን ስም ጋር

የተቀላቀሉ ዴባል የሰው ስሞች የማዕረግ ስሞችን የምንለብስ ከሆነ እውነትኛ ክርስቲያን አይደለንም ማለት ነው፡፡ክርስቲያን የሚለው ስም አንዱን ከሌላው ዓለም የሚለየውና እግዚአብሄር ያወጣልን ስም መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡

በሁለቱም በቤተክርስቲያንና በክርስቲያን ስም መጠሪያ የክርስቶስ ስም ከፍ ከፍ ይላል፡፡ ለምን? ምክንያቱም የቤተሰብ ስም ነው (ኤፌሶን 3፡14~15)፣ ከስሞች ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያለ ስም ነው (ፊሊጲሲዮስ 2፡ 9~11)፣ መዳን በሱ ብቻ የሚገኝበት ነው (ሓዋርያት 4፡12)፣ ስለዚህ በክርስቶስ ስም እናምናለን ( 1ኛ ዮሃንስ 5፡13)፣ ያንን ስም እንመሰክራለን ( 1 ኛ ጢሞቴዎስ 2፡19) በስሙ ንሰሓ ገብተን እንጠመቃለን (ሓዋርያት ሥራ 2፡38)፣ በዚያ ስም ለአምልኮ እንሰበሰባለን (ማቴዎስ 18፡20)፣ ሁሉን ነገር በዚህ ስም እናደርጋለን (ቆላስያስ 3፡17) በዚህ ስም የዘላለምን ህይወት እናገኛለን (ዮሃንስ 20፡30~31)፡፡

ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት ማንም ሰው በስም ውስጥ ምንም ነገር የለም ሊል አይችልም፡፡ በሰዎች ስምና ማዕረግ መዳን ፈጽሞ የለም ነገር ግን ያንን የሰው ስምና ማዕረግ የለበሱት በነርሱ ምክንያት ይጠፋሉ፡፡ በሌላ በኩል መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

## ጥያቄዎች

### የጎደለ ቦታ ሙላ

1. ቤተክርስቲያን መጽሃፍ ቅዱሳዊ_____________________________________ ሊኖራት ይገባል
2. ሰው ሰራሽ ስሞችና ማዕ ጎች_______________________________________ ናቸው
3. የ______________________________ጸሎት__________________ ለማክበር ነው
4. አሁን አንተ ______________________________________ነህ
5. እግዚአብሄር ለህዝቡ________________________________ ሰጥቶአል

### አዎን ወይም አይደለም ብለህ መልስ

1 መጽሃፍ ቅዱሳዊ የሆነች ቤተክርስቲያን መጽሃፍ ቅዱሳዊ ስም ሊኖራት ይገባል________

2 ሰው ሰራሽ ስሞችና ማዕረጎች ስህተት ናቸው?_________________

3 ጌታ ባሁኑ ዘመን ተመሳሳይ ስም እንድንለብስ

ይፈልጋል?___________________
4 አንድ ሰው የክርስቶስን ስም ካልለበስ እሱን ሊያከብር ይችላል?____________
5 መዳን በክርስቶስ ስም ብቻ ነው?________________________________

## ትክክለኛውን መልስ መልስ

1. ሰው ሰራሽ ስሞች እንዴት ሊመጡ ቻሉ?________________
2. ሰው ሰራሽ ስሞችና ማዕረጎች ስህተት የሆኑበት ምክንያቶችን ጥቂት ዘርዝር_______________________________________________
3. ክርስቶስ ስለምን ነበር የጸለየው?__________________________________________
4. ወንድሞች በተከፋፈሉበት ጊዜ ጳውሎስ ያደረገውን ተናገር ____________________________________
5. ቤተክርስቲያን የክርስቶስን ስም መልበስ ያለባት ለምንድ ነው?___________________________________
6. ሮሜ 16፥16 ጥቀስ__________________________________________________
7. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥27 መሰረት አካል ምንድ ነው?______________________________________
8. የቤተክርስቲያን ሌሎች ስሞችን ግለጻቸው_____________________________
9. ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ካልሆነች የማን ልትሆን ትችላለች?_____________
10. የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ምን ተብለው ይጠራሉ?_______________________________
11. ስለክርስቲያን የሚገልጽ ሶስት ጥቅሶችን ግለጥ_______________________________________
12. ጌታ ዛሬ ምን እንድንሆን ይፈልጋል?____________________________________________
13. እንዴነዝያ ግዜ ክርስቲያን መሆን አሁን ይቻላል?__________
14. የክርስቶስን ስም ከፍ ከፍ የምናደርገው ለምንድነው?_____
15. በክርስቶስ ስም ምን ምን እናደርጋለን?__________________

## ትምህርት ስድስት
## የቤተክርስቲያን አደረጃጀት

ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መሰረተ። (ማቴዎስ 16፡18), ያቺ ቤተክርስቲያን የተጠሩ ሰዎች ስብስብ ኖት,ከዓለም የተጠሩ (ቆሮንቶስ 1፡13,14) የዳኑ ሰዎች ስብስብ (ሐዋርያት ሥራ 2፡47) የክርስቶስ መንፈሳዊ አካሉ ናት (ቆላስያስ 1፡18) እሷም አንዲት አካል ናት (ኤፌሶን 4፡4)

ቤተክርስቲያን በተፈጥሯ ውስጥ ሁለንተናዊ ስትሆን ወይም ሁሉን አቀፍ ስትሆን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በግል ጉዳዮች ያላት ሲሆን እያንዳንዱ ማህበር ብዙ አባላት ያቀፈ ነው። ይህ ማለት የቤተክርስቲያን መንግስት የሃገር ውስጥ እንጂ ቢሔራዊ ወይም አለም አቀፋዊ አይደለም ማለት ነው። በለላ አነጋገር የጌታ ቤተክርስቲያን ምድራዊ ወይም በምድር ዋና መሥሪያ ቤት የላትም ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ይናገራል። እስቲ የሚቀጥለውን ጥቅስ እንመልከት። “ሁሉም ከእግሩ በታች አስገዛላት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተክርስቲያን ሰጠው እርሷም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት” ይላል (ኤፌ 1፡22~23)። “ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን እንደሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና”(ኤፌሶን 5፡ 23) “እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው። እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው” (ቆላስያስ 1፡ 18) አሁን እነዚህ ጥቅሶች ምን ያስተምራሉ? እንደተጠቀሰው ክርስቶስ የአካሉ ራስ ነው, ቤተክርስቲያን ዬትኛዋ ናት ስንት ራሶች እዚያ አሉ? አንድ ብቻ ያም አንድ ክርስቶስ ብቻ ሲሆን ይህንን ለማንም አያጋራም። ቤተክርስቲያን ብዙ ማህበሮች ያላት ሲሆን ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደመሆኑ የሁሉም ጉባኤ ራስ እሱ ብቻ ነው። እንደዚሁም የእያንዳንዱ የማህበር አካላት ራስም ነው። ይህንን ጳውሎስ ሲያብራራ “ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትምራስ ወንድ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ ይገባል” ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡3)

ቀጥሎ እያንዳንዱ የአካባቢ ማህበር የራሱ አደረጃጀት አለው። ክርስቶስ አባት በሽማግሌዎች እና በዲያቆናት መካከል ራስ ሆኖ የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ እና ሥጋዊ ፍላጎቶች እንዲመለከቱ ይሾማቸዋል። ሽማግለዎቹ የአባቱን ነፍሳት መጠበቅ አለባቸው (ዕብራውያን 13፡7) ዲያቆናት የነገሮችን ሥጋዊ ገጽታ መጠበቅ አለባቸው (ሐዋርያት 6)። ቅዱሳት መጽሐፍት አንድ ሽማግለና አንድ ዲያቆን ከመግዛት ይልቅ በእያንዳዱ ጉባኤ ላይ ስለብዙዎች

ሽማግለዎቻችና ዲያቆናት እንደሚናገሩ ልብ በል። ጉባኤዎቻ እርስ በራሳቸው ይተባበራሉ እንጂ በሌላው ጉባኤ ላይ አይቆጣጠሩም።

ሽማግሌ፣ፓስተር፣ኤጲስ ቆጲስ እረኛ እና ፕረስባይተር የሚሉት ቃላቶች አንድ አይነት ቢሮ አላቸው። ስለዚህ ቸማግሌ ፓስተር፣ጳጳስ ወዘተ....ነው። በ 1ኛ ጢሞትዮስ 3፡1~7 ላይ ጳውሎስ ስለመስፈርቶቹ ቁጥሮች ሲገለጽ "ማንም ኤጲስ ቆጲስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጲስ እንዲህ ሲሆን ይገባዋል። የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል ልከኛ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የሚሰራ እንግዳ ተቀባይ ለማስተማር የሚበቃ የማይሰክር፣የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ የማይከራከር ገንዘብን የማይወድ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር ሰው ግን የራሱን እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃል? በትቤዕት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያ አይሁን። በዲያብሎስ ነቀፋና ወጥመድም እንዳይወድቅ በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባል። ይህ መስፈርት በቲቶ 1፡5~9 ላይም ተገልጽዖአል።ስለዚህ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ማንኛውም ሰው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሊሆን አይችልም። ብቁ የሆኑትን ብቻ መሾም ይገባል።እናም በቁጥር ከአንድ በላይ መሆን አለባቸው። ሽማግለ ለመሆን ብቁ የሆኑ አባል በሌሉበት ጉባኤ እስኪያድጉ ድረስ የቤተክርስቲያኑ ሰዎች የቤተክርስቲያኒቱን ጉዳይ ሊከታተሉ ይገባል።

ከሽማግሌዎች ጋር የሚያገለግሉ ዲያቆናትም ይሾማሉ። አገልጋዮች በመባልም ይታወቃሉ። እናም በአካባቢው  ሽማግሌዎች አመራር ሥር ይሰራሉ። ጳውሎስ ስለዲያቆናት ሹመት መስፈርቱን ሲነግረን "እንዲውም ዲያቆናት ጭምቶች በሁለት ቃል የማይናገሩ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ ነውረኛ ረብ የማይወዱ በንጹህ ህሊና የሃይማኖት ምስጥር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል። እነዚህም ደግሞ አስቀድመው ይፈተኑ ከዙያም ቦኃላ ያለ ነቀፋ ቢሆን በዲቁና ሥራ ያገልግሉ። እንዲሁም ሴቶች ጭምቶች የማያሙ ልከኞች በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል፣ ዲያቆናት ልጆቻቸውንና የራሳቸውን ቤቶች በመልካም እየገዙ እያንዳንዳቸው የአንዲት ሴት ባል ይሁኑ። በዲቁና ሥራ በመልካም ያገልግሉ፣ ለራሳቸው ትልቅ በክርስቶስ ኢዬሱስ ባለው እውነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ" (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡8~11)።

አሁን ይህ የቤተክርስቲያን መለኮታዊ አደረጃጀት ነው። ክርስቶስ ራስ ነው እያንዳንዱ ጉባኤ የራሱ ሽማግሌዎቻችና ዲያቆናት አሉት ። በነርሱ ሥልጣን ሥር ሰባኪዎቻ እና አስተማሪዎቻ እና አባላት ይኖራሉ ከጌታ መንገድ አንዱ ከጉባኤ ወጥቶ ወደ  ስህተት ትምህርት ቢገባ ሌሎቹ በታማኝነት ሊቀጥሉ ይቻላሉ። ወይም ሁሉም ጉባኤ ከእውነት

ቢወጣ አንድ ብቻ ታማኝ ሊሆን ይችላል። እናም ለዚያ ታማኝ ታማኝ መሆን አለባቸው። በጌታ አደረጃጀት እያንዳንዱ ጉባኤ ራሱን የቻለ ነው። በአንድ ላይ የሚተሳሰሩት በሰው ሰራሽ ህግ ሳይሆን በፍቅር ነው። ስለዚህ እርስበርሳቸው ኅብረት አላቸው። በክርስቶስም አንድ ሆነው አብረው ይሰራሉ። የጌታ መንገድ በሰው ሊሻሻል አይችልም።

በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ዬትም ቦታ ጴጥሮስ ወይም ሌላ ሰው የቤተክርስቲያን ራስ ነው የሚል አታነብም። ዬትም ቦታ ኤጵስቆጶስ ፓስተር ወንጌላዊ የማህበሩ ራስ ነው የሚል አታነብም ቁሳውስትም ሆነ ምዕመናን የቤተክርስቲያን ራስ የሚል አታነብም። አብዛኛው የሃይማኖት ድርጅት ዓለም እግዚአብሄር ለቤተክርስቲያን ካስቀመጠው ተዕዛዝ ወጥተዋል። ይህም ለቤተክርስቲያን መለያየት ምክንያት አንዱ ሆኖአል። እንግዲውስ ለቤተክርስቲያን አደረጃጀት እውነተኛውን የቅዱሳት መጽሃፍት ንድፍ ወደ ሆነው ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ለመመለስ ዛሬውኑ እንወስን።

## ጥያቄዎች
## ትክልለኛውን መልስ ስጥ

1.ቤተክርስቲያንን የመሰረተው ማን ነው?

2. ቤተክርስቲያን የተዋቀረቸው ከምንድነው?

3.የክርስቶስ አካል መንፈሳዊ ነው ወይስ ሥጋዊ?

4.ስንት ቤተክርስቲያን አሉ?

5. ቤተክርስቲያን በተፈጥሮዋ ________________________________________ ነች

6.ቤተክርስቲያን በመቶ ሺዎች የግል ጉባኤ________________________________ ነች

7.የቤተክርስቲያን መንግስት ቢሄራዊ እና አለም አቀፋዊ ናት?

8.የጌታ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ራስ ወይም ዋና ምሥሪያ ቤት አላት?

9.የቤተክርስቲያን ራስ ማን ነው?

10.ቤተክርስቲያንን የሚመሩት ምን ይባላሉ?

11.የሽማግሌዎች እና የዲያቆናት ሥራ ምንድነው?

12.ስንት ሽማግሌዎች እና ዲያቆናት ለአንድ ቤትክርስቲያን ያስፈልጋሉ?

13.የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሌላ ስያሜ ምን ተብለው ይጠራሉ?

14.የሽማግሌዎችን መስፈርት ዬት ቦታ እናገኛለን?

15.የዲያቆናት ሹመት መስፈርት ዬት ቦታ እናገኛለን?

16.ለሹመት ብቁ ሰው ከሌለ ቤትክርስቲያን ሽማጊሌ ሊኖራት ይቸላል?

17.ይህ በሚሆንበት ጊዜ ማን ነው የሚመራት?

18.ቤተክርስቲያን አብረው የምተሳሰሩት በምንድነው?

19.የእግዚአብሄርን መንገድ ማሻሻል ይቻላል?

20.እንደቅዱሳት መጻሕፍት ጴጥሮስ የቤተክርስቲያን ራስ ንው?

21.በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ጳጳስ የሚባል ሰው በብዙ መዕመናን ላይ ስለተሾመባት ቢሮ እናነባለን?

22.ፓስተር ወይም መጋቢ በአንዲት ቤተክርስቲያን ላይ እንዳለ እናነባለን?

23.በመጻሓፍ ቅዱስ ውስጥ ስለቀሳውስት እናነባለን?

24.በዓለም ላይ ብዙ መለያየት የተፈጠረው ለምንድነው?

25.ለቤተክርስቲያን አደረጃጀት ንድፍ ለማግኘት ወደዬት መሄድ አለብን?

## ትምህርት ሰባት
## ወደ ቤተክርስቲያን ለመግባት

እስካሁንባለውጥናታቸንየቤተክርስቲያንአስፈላጊነትንአይተናል፡፡ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን መሞቱን ቅዱሳት መጽሃፍት የሚያስተምሩት ነው፡፡ (ኤፌሶን 5፡25) በደሙ ነው የዋጃት (ሓዋርያት ሥራ 20፡28) እሱ አዳኛዋ ነው (ኤፌሶን 5፡23)፡፡ እንግዲህ እነዚህ ጥያቄዎቸ ሊነሱ ይቸላሉ፡፡ ክርስቶስ አስፈላጊ ላልሆነ ነገር ነው የሞተው? ደሙን ያፈሰሰውስ ዋጋቢስ ለሆነ ቤተክርስቲያን ነው? ክርስቶስ ከሞተላት ቤተክርስቲያን ውጪ መዳን ይቻላል? በእውነት ለሁሉም ጥያቄዎቸ መልስህ አይደለም የሚል ይሆናል፡፡ ታዲያ ለምንድነው ቤተክርስቲያን አስፈላጊ አይደለቸም እና አንድ ሰው የርሱዋ አባል ሳይሆን መዳን ይቸላል የሚባለው? እንዲያው እንደነዚህ ዓይነት ሰዎቸ ስለቤተክርስቲያን መረዳት የሌላቸው እና የተታለሉ ብቻ ናቸው፡፡

በርግጥ መጽሓፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን አዳኝ እንደሆነቸ አላስተማረም፡፡ ነገር ኘ በተመሣሣይ ጊዘ አንድ ሰው ለመዳን በቤተክርስቲያን ውስጥ መሆን እንዳለበት ያስተምራል፡፡ መርከቡ አዳኝ እንዳልነበረ ሁሉ ኖህ እና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ ለመዳን በመርከብ ውስጥ መሆን ነበረባቸው፡፡ ቤተክርስቲያንም እንደሁ ናጥ ህዝቡም በበአለ ሃምሣ ቀን ወንጌልን ሰምተው ሲታዘዙት እና ቦኃላ ባሉት ቀናት የሆነውን በእግዚአብሄር ቃል የተመዘገበው እንድህ ይላል “ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር” ይላል (የሓዋርያት ሥራ 2፡47)፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ሲድን የቤተክርስቲያን አባል ይሆናል፡፡

የቤትክርስቲያን አባል ያልሆነ አልዳነም ማለት ነው፡፡ ይህ ቀላል ነገር ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ከቤተክርስቲያን ውጪ መዳን የሚባል ነገር የለም፡፡ በሰዎች ቡድን በሃይማኖት ዓለም ይሆን ይሆናል፡፡ ነገር ግን የክርስቶስ ቤትክርስቲያን አባል ካልሆን ሊድን አይችልም፡፡

ጥናታችንን በመቀጠል የጌታን ቤተክርስቲያን መቀላቀል አይቻልም ይልቁንም ጌታ የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምራቸዋል፡፡ በቤተክርስቲያን ላይ የዳኑትን ብቻ ስለሚጨምር ቤተክርስቲያን በዳኑት ሰዎች የተዋቀረች ናጥ ጌታ ከልብ የሚታዘዙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሰውዬውን ድርጊት የሚያመነጩትን ልብ ውስጣዊ ምንነቱን ወዘተ ይመለከታል፡፡ ቅን ስለሆነ ብቻ ወደ ቤተክርስቲያን ይጨመራል ብለን እኛ ብናስብ እንኳን እግዚአብሄር ካልጨመረ አልተጨመረም፡፡ ምክንያቱም እኛ ውጫዊ ታዛዥነቱን እንጂ ውስጣዊ የልቡን ስለማናይ ነው፡፡ በሃይማኖቱ ዓለም ግን ማንም ሰው ለመቀላቀል ዓላማው ምንም ይሁን ምን መቀላቀል ይችላል፡፡ በጌታ ቤተክርስቲያን ግን ለመጨመር አስፈላጊውን ካሟላ ብቻ ሲሆን ያንንም የሚጨምረው ጌታ ብቻ ነው፡፡ ለያንዳንዱ ነፍሳት ወደ ቤትክርስቲያን መጨመር ተጠያቂ ጌታ ብቻ የሚሆንውም ለዚህ ነው፡፡ ከዳኑት መካከል ማን ምን እንደሆነ ምን መሆን እንዳለበትም ጌታ ብቻ ያውቃል፡፡

ክርስቶስ የቤተክርስቲያን አዳኝ ከሆነ እና ወደ ቤተክርስቲያንም የሚጨምር እሱ ብቻ ከሆን የሚጨምራቸውም የዳኑትን ብቻ ከሆነ የግድ እንደ ጌታ ፈቃድ ወደ ጌታ ቤተክርስቲያን ለመግባት እሱ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ማሟላት የሚገባቸውን ደግሞ በግልጽ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡

በተለይም ይህ በሓዋርያት ሥራ መጽሃፍ ውስጥ በግልጽ ይነበባሉ እነዚህንም አሁን ወደ ቤተክርስቲያን የመግቢያ መስፈርቶችን ወይም ደረጃዎችን ልብ ይበሉ፡፡

1. አንድ ሰው እውነትን መስማት አለበት "እምነት ከመስማት ይመጣል መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው" (ሮሜ 10፡17)

2. በእግዚአብሄር እና በክርስቶስ ማመን አለበት ፡፡ "ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም ወደ እግዚአብሄር ለመድረስ እግዚአብሄር እንዳል ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል" (ዕብራዊያን 11፡6)፤ "ልባቸሁ አይታወክ በእግዚአብሄር እመኑ በእኔም እመኑ" (ዮሃንስ 14፡1)

3. ከኃጥያቱ ንሰሃ መግባት አለበት "እላቸዋለሁ አይደለም ነገር ግን ንሰሃ ባትገቡ ሁላቸሁ እንዲሁ ትጠፋላቸሁ" (ሉቃስ 13፡3)

4. ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መመስከር አለበት ክርስቶስ እንዲህ አለ "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔ ደግሞ በሰማይ አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ" አለ (ማቴዎስ 10፡32)፡፡

5. ለኃጥያቱ ስርዬት መጠመቅ አለበት “ጥምቀቱ በመቀበር መሆን አለበት (ሮሜ 6፡3፡4፤ የሐዋርያት ሥራ 8፡2~39” “ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል” (ማርቆስ 16፡16) “ጴጥሮስም ንሠሃ ግቡ ኃጥያታቸሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳቸሁ በኢዬሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላቸሁ” አላቸው (የሐዋርያት ሥራ 2፡38)

በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ላይ ምን ነበር የተማርነው? ክርስቶስ የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያን መጨመሩን ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ሰው ጌታን ታዞ ሲድን ወድያውኑ በጌታ ቤተክርስቲያን ላይ ይጨምራል፡፡ መልካም ! እናም ያየነው እውነትን በመስማት፤ በማመን፤ ከኃጥያቱ ንሠሃ በመግባት ፤ ክርስቶስን በመመስከር እና በመጠመቅ አንድ ሰው ይድናል፡፡ ማንኛውም ሰው በግሉ ይህንን ሲያደርግ ቤተክርስቲያን ላይ ይጨመራል፡፡ እንግዲህ ይህ የእግዚአብሄር ለድህንነታችን እቅድ ከሆነና ጌታ ደግሞ ስንድን ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚጨምር ከሆን ይህ ቀላል አይደለም?

ሌላ የመጨመር መንገድ ጌታ እንደተናገረው አንድ ሰው ወደ እግዚአብሂር መንግስት ለመግባት ከውሃ እና ከመንፈስ ሲወለድ ነው (ዮሃንስ 3፡3~5) ፡፡ ነገር ግን መንግስት ምንድነው? እሱ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ (ማቴዎስ 16፡18~19)፡፡ መልካም ! ጌታ ሰዎቸ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲገቡ ሁለት መንገዶቸ አሉት? በርግጥ ሁለት መንገዶቸ የሉም፡፡ ታዲያ አንድ ሰው አምኖ ሲጠመቅ (በቃሉ በመንፈስ ተወልዶ ትምህርቱን በመታዘዝ) ከዚያም በእግዚአብሄር መንግስት ወይም በእግዚአብሄር ቤተሰብ በጌታ ቤተክርስትያን ውስጥ ይወለዳል፡፡

በድጋሚ ጳውሎስ “. አንድ አካል ለመሆን ተጠምቀናል “ ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13) ግን ያ አካል ምንድነው? ያ አካል ቤተክርስቲያን ነው (ቆላስያስ 1፡18) ስንት አካል ናቸው? (አንድ አካል ነው (ኤፌሶን 4፡4፤ ኤፌሶን 1፡22~23) አንድ ሰው እንዴት ይገባባታል? በጥምቀት ክርስቶስ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ብሏልና (ማርቆስ 16፡16) መልካም ! ይህ ደግሞ የቆሮንቶስ ሰዎቸ እንዳደረጉት ነው (ሐዋርያት ሥራ 18፡8) ስለዚህ አንድ ሰው በቤተክርስቲያን ከተጠመቀ የቤተክርስቲያኒቷ አካል ይሆናል ወይም በቤተክርስቲያን ላይ ይጨመራል፡፡

ለመዳን ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነው፡፡ እንዳየነውም ጌታ የሚድኑትን በቤተክርስቲያን ይጨምራቸዋል፡፡ እዚህ በመጽሃፍ ቅዱስ ያነበብከው ቤተክርስቲያን አባል ነህ? ካልሆንክ አልዳንክም፡፡ ቃሉን መርምር አጥና ታዘዝ ከዚያ ጌታ በቤተክርስቲያኑ ላይ ይጨምርሃል፡፡

## ጥያቄዎች
## ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ስለ ቤተክርስቲያን ጥናታችን ምን ምን አየን?
2. ለቤተክርስቲያን የሞተው ማን ነው?
3. ቤተክርስቲያን የተገዛቸው በምንድነው?
4. የቤተክርስቲያን አዳኝ ማን ነው?
5. ቤተክርስቲያን አስፈላጊ መሆኗን እንዴት እናውቃለን?
6. አንዳንዶች ቤተክርስቲያን አያስፈልግም ለምን ይላሉ?
7. ቤተክርስቲያን ታድናለች?
8. አንድ ሰው ለመዳን የቤተክርስቲያን አባል መሆን አለበት?
9. ኖህ እና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ የዳኑት ዬት ነበር?
10. ከመርከብ ውጪ የሚድኑበት ነገር ነበር?
11. የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያን የሚጨምር ማን ነው?
12. ይህንን የሚያስተምር ጥቅስ ስጥ
13. አንድ ሰው ከዳን በኋላ ወዲያውኑ የሚጨመረው በዬትኛው ቤተክርስቲያን ነው?
14. አንድ ሰው የጌታን ቤተክርስቲያን መቀላቀል ይቸላል?
15. አምስቱ ወደ ቤተክርስቲያን መግቢያ መስፈርቶች ምን ምን ናቸው?
16. አንድ ሰው እነዚህን መስፈርቶቸህ ሳይታዘዝ መዳን ይቸላል?
17. ጥምቀት ምንድነው?
18. የጥምቀት ዓላማው ምንድነው?
19. መንግስት ምንድነው?
20. ወደ መንግስት መግቢያ ብቸኛ መንገድ ምንድነው?
21. አካል ምንድነው?
22. ስንት አካሎች አሉ?
23. አንድ ሰው እንዴት ዩገባባታል?
24. ለመዳን ስንት መንገዶች አሉ?
25. ብቤተክርስቲያን ለመጨመር ስንት መንገዶች አሉ?

## ትምህርት ስምንት
## የቤተክርስቲያን አምልኮ

ቤተክርስቲያን በዳኑት ሰዎች የተዋቀረች ናት ፡፡ ዓላማው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሄርን ማምለክና ማገልገል ነው፡፡ጳውሎስ ሲናገር "እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉ" ይላል፡፡ (ቆላስያስ 3፡17)

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት አይነት አምልኮዎች አሉ፡፡ አንደኛ የምናነበው ያለዕውቀት አምልኮ ነው፡፡ ጳውሎስ በአቴና በነበረበት ጊዜ የተመለከተው ብዙ ጣኦታትን አይቶ "የምታመልኩትን እየተመለከትኩ ሳልፍ ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽህፈት ያለበትን መሰዊያ ደግሞ አይቻለሁናእንግዲህይህንሳታውቁየምታመልኩትንእኔእንግራችዋለሁ " አላቸው (የሓዋርያት ሥራ 17፡23) እንደዚሁ ያለዕውቀት ሲያመልኩ እንደነበር ሁሉ ዛሬም ያለዕውቀት የሚያመልኩ አሉ፡፡ ለጣኦታት እና ለምስሎች የሚንበረከኩ ሚሊዮኖች ብቻ አይደሉም ነገር ግን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የሃይማኖታዊ ልምምዶች መጽሃፍ ቅዱስን ካለ ማወቅ የተነሳ ሲያመልኩ ይታያሉ፡፡ ሁለተኛው የጌታ ቃል ሲናገር በከንቱ ስለሚያመልኩ ሲጠቅስ ክርስቶስ እንዲህ ይላል "የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል" ይላል (ማቴዎስ 15፡9)፡፡ በዛሬው ጊዜ አብዛኛው ሰው የሚያመልከው በዚህ መንገድ ነው፡፡ ጌታን ያመልኩታል እውነት ነው ነገር ግን አምልኳቸው ከንቱ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደእግዚአብሄር ፈቃድ ሳይሆን እንደሰዎች ትምህርትና ወግ ነው፡፡ ሦስተኛው የእግዚአብሄር ቃል እንደሚናገር ስለ እውነተኛ አምልኮ ነው፡፡ ያም በእውነትና በመንፈስ የሆነ አምልኮ ነው፡፡ የክርስቶስን ቃል ስናነብ "እግዚአብሄር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" ይላል (ዮሃንስ 4፡24)፡፡ ይህ ብቸኛው በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ያለው አምልኮ ነው፡፡ ይህ በክርስቶስ ዘመን አሁን በኛ ዘመን እውነተኛ የሆነው አምልኮ ነው፡፡ይህ በመንፈስ በቀጥታ ወደ እግዚአብሄር የሚደርስ በትህትና እና በመረዳት የሆነ አምልኮ ነው፡፡ (በእውነት) የሚለው ደግሞ እንደቃሉ መሰረት እንደተጻፈው ማምለክ ማለት ነው፡፡እግዚአብሄር ማንንም እንዲያመልኩት አያስገድድም ነገር ግን እናመልካን የሚሉት እንደሱ ፈቃድ እና በተጻፈው መሰረት እንዲያመልኩት ይፈልጋል

የጌታ ቤተክርስቲያን ምን ዓይነት አምልኮ ነው የምትፈልገው? በእርግጠኝነት ያለዕውቀት አምልኮ አይደለም፡፡ እንደሰዎች ትምህርትና ተዕዛዝም ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንም በመንፈስና በእውነት በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ነው እንጂ፡፡ በአዲስ ኪዳን

ስናይ የቀደመቹው ቤተክርስቲያን በነዚህ አምስት የአምልኮ ሥራዓቶች ላይ ተመስርታ አምልኮዋን እንደምትፈጽም በቀጥታ ከመጽሃፍ ቅዱስ እንመለከታለን

1. ቃልን ለማጥናት ይሰበሰባሉ ጢሞተዎስም ከህጻንነቱ ጀምሮ ቅዱሳት መጽሃፍትን አውቋል (2 ጢሞቴዎስ 3፡15) ጳውሎስ ወጣት ሰባኪውን ያበረታተዋል፡፡"የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍር ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሄር ልታቀርብ ትጋ" ይለዋል (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15)፡፡ ይህ ለሁሉም ክርስቲያን በተለይ ለአምልኮ ለሚሰበሰቡት ሁሉ ይሠራል፡፡ ይህ ጊዜ እግዚአብሄር ለልጆቹ በቃሉ በኩል የሚናገርበት ጊዜ ነው፡፡ በሓዋርያት ሥራ 20፡7 የምናነበው ወንድሞች ተሰባስበው ጳውሎስ ቃልን ሲስብካቸው እናነባለን፡፡

2. በመጸለይ ያመልካሉ በጴንጤቆስጤ ቀን ሰዎች ወንጌልን እንደታዘዙ የምናነበው "በሃዋርያት ምትምህርትና በኅብረት እንጀራንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር (የሓዋርያት ሥራ 2፡42) በጸሎት አማካኝነት የእግዚአብሄር ህዝብ በሰማይ ላለው አባታቸው የመናገር ዕድል አላቸው፡፡ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ለአምልኮ ለመሰባሰብ ዱሩ ግን ላልመጸለይ እንዴት ይታሰባል?

3. መዝሙር በመዘመር ያመልካሉ ጳውሎስ ሲጽፍ "በመዝሙርና በመንፈሳዊ ቅኔ እርስበርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ" ይላል (ኤፌሶን 5፡19) እንደዚሁም ቆላስያስ 3፡16፣ ዕብራዊያን 13፡15 አንብባቸው፡፡ ሁለት ዓይነት ሙዚቃ አሉ፡፡ አንደኛው በሰው ድምጽ ሲሆን ሁለተኛው በመካኒካል ነው፡፡ እግዚአብሄር የሚፈልገው ምን ዓይነት ሙዚቃ ነው? እግዚአብሄር የሚጠይቀው በድምጽ የሆንውን በሰው ድምጽ የሆነውን ነው፡፡ ጳውሎስ በልባችን ዜማ ለጌታ እንድንቀኝ ይናገራል፡፡ የጳውሎስ ቃል ግልጽ ነው፡፡ መካኒካልን ማለቱ አይደለም፡፡ የጥንቲቷ ክርስቲያኖችም እግዚአብሄርን በድምጻቸ ይዘምሩ ያመልኩ ነበር፡፡ ከዘመናት ቦኃላ ሰዎች መካኒካል ሙዚቃን ጀመሩ ቢሆንም እግዚአብሄር ይህንን የሙዚቃ መሳሪያ አልፈቀደውም አይቀበለውምም፡፡ ክርስቲያኖች አምላክን በድምጻቸው ከማመስገን በቀር በመካኒካል ሙዚቃ ማመስገን አይችሉም፡፡

4. የጌታ እራትን በመውሰድ ያመልካሉ ይህንን በሓዋርያት ሥራ 20፡7 ላይ ምሳሌ አለን፡፡ በማቴዎስ 26፡26-28 እና በ 1ኛ ቆሮንቶስ 11 ላይ የተማርነው ለጌታ መታሰቢያ ሥጋውን ለማሰብ የሥጋው ተምሳሌት የሆነውን እብስት እንቆርሳለን የደሙ ተምሳሌት የሆንውን ጽዋ ከወይን ጭማቂ የሆነ የደሙን መታሰቢያ እንወስዳለን እንካፈላለን ይህም በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን በመሰባሰብ በዚህ መልኩ እናመልካለን፡፡

5. በስጦታ ያመልካሉ ጳውሎስ የቆሮንቶስ እና የጋላቲያ ወንድሞችን ሲያዝ እንዲህ ይላል "እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት

ያን ጊዜ እንዳይሆን ከናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ " (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2) እንዲሁም 2ኛ ቆሮንቶስ 9፡7ን ያንብቡ።

የጥንቷ ክርስቲያኖች በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ይሰበሰባሉ (የሓዋርያት ሥራ 20፡7፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2) ጌታን ያመልካሉ። ይህን አስመልክቶ የዕብራዊያን ጸሃፊ ሲያስጠንቅቅ እንድህ ይላል "በአንዳንዶቹም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስበርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ" ይላል (ዕብራዊያን 10፡25) የዛሬዋ የኛም በተመሳሳይ ሁኔታ በተመሳሳይ ቀን ጌታን ለማምለክ እንሰበሰባለን ይህ ማጠንቀቂያ እኛንም ይመለከተናልና።

የቤተክርስቲያን አምልኮ በጣም ቀላልና ብዙዎቹ በቀላልነቱ ይሰናከላሉ። ረጅም መሆን አለበት ብለው ያስባሉ በብዙ ወኛ ሥራዓት ለአንድ ነጠላ ተግባራት በጸሎት ድግግሞሽ ያስረዝማሉ። ነገር ግን እንደዚያ አይደለም። እግዚአብሄር በአምልኮ ላይ ፈቃዱን ገልጿል። ለሰዎች የመለወጥ ሥልጣን አልተሰጣቸውም። ይህ በእግዚአብሄር ፈቃድ እና በተጻፈው ላይ በተቃራኒ ሆኖ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ሲሆን ይህ ደግሞ የጌታን እርግማን ያስከትላል (ዮሃንስ ራዕይ 22፡1~19) እግዚአብሄር ተናግሯል። እሱ የተናገረው ደግሞ በመጽሃፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል ስለዚህ ህዝቡ መታዘዝ አለባችሁው ያን ጊዜ ብቻ ነው እግዚአብሄር በትክክል ሊመለክ እና ሊመሰገን ሊከብርም የሚቻለው።

## ጥያቄዎች

### ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ቤተክርስቲያን የተዋቀረቸው ከምንድነው?
2. የቤተክርስቲያን ዓላማ ምንድነው?
3. በጌታ ስም ምን ምን ይደረጋሉ?
4. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስንት ዓይነት አምልኮ አነበብን?
5. ጳውሎስ ጣኦታትን የተመለከተው ዬት ነበር?
6. ስለነሱ አምልኮ ምን ነበር ያለው?
7. በዛሬው ዘመን እንደነሱ የሚያመልኩ አሉ?
8. ማነው እግዚአብሄርን በከንቱ ያመልካሉ ያለው?
9. አምልኳቸው ከንቱ የተባለው ለምንድነው?
10. ይህንን የሚገልጽ ጥቅስ ጥቀስ
11. በዚህ ዘመንስ ጌታን በከንቱ የሚያመልኩ አሉ?
12. አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው?
13. ዮሃንስ 4፡24 ጥቀስ
14. እግዚአብሄርን በመንፈስ ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው?

15. እግዚአብሄርን በእዉነት ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው?
16. እግዚአብሄር ከህዝቡ የሚፈልገው ምን ዓይነት አምልኮ ነው?
17. የእግዚአብሄር ሰዎች ጌታን የሚያመልኩትን ዬት ውስጥ እናገኛለን?
18. አምስቱን የአምልኮ ዓይነት ግለጽ
19. እግዚአብሄር ዛሬ ለህዝቡ የሚናገረው እንዴት ነው?
20. የእግዚአብሄር ልጆች ለእግዚአብሄር የሚናገሩት እንዴት ነው?
21. ሁለት ዓይነት ሙዚቃ ምንድናቸው?
22. እግዚአብሄር የሚፈልገውን ሙዚቃ ዓይነት ዬትኛው ነው?
23. የጌታ እራት ምንድነው?
24. በሳምንቱ በዬትኛው ቀን ክርስቲያን ይሰበሰባሉ?
25. እግዚአብሄር ስለአምልኮ ባለው እቅድ ላይ ሰዎች መጨመር ወይም መቀነስ ይችላሉ?

## ትምህርት ዘጠኝ
## የቤተክርስቲያን ሥራ

ቤተክርስቲያን ለምን ትኖራለች? ዓላማዋ ምንድነው? ሥራዋስ ምንድነው? እነዚህን መልሶች ለማግኘት ወደ መጽሃፍ ቅዱስ የእግዚብሄር ቃል መሄድ አለብን።

በመጀመሪያ ደረጃ ቤተክርስቲያን ዓለማዊ የንግድ ሥራ አይደለችም። ትምህርት ቤት አይደለችም ወይም ሆስፒታል እንዳልሆነች እናስተውል። ገንዘብ ለማግኘት ሲባል በህትመትና በመትሃፍ ሽያጭ ላይም አሰማራም። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ጥሩ ሊሆኑ ቢችሉም እናም እያንዳንዱ ክርስቲያን በርግጥ በነዚህ ነገሮች ላይ የመሳተፍ መብት ቢኖረውም የቤተክርስቲያን ሥራ ግን በንደዚህ ዓይነት ነገሮች ሊጻተፍ አትችልም። ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን ሃይማኖታዊው ዓለም በንደዚህ ዓይነት ተግባር እና እንደ ዓላማም ሲያደርጉት ይታያል ይህ ደግሞ የእግዚአብሄርን ቃል የሚቃረን ነው።

ወደ እግዚአብሄር ቃል መጥተን ስንመረምረው እንደቃሉ የቤተክርስቲያን ሥራ በሦስት መንገዶች ይገለጻል። እነዚህም ወንጌልን መስበክ፤ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ማድረግ እና ቅዱሳንን ማነጽ ናቸው። እነዚህንም አንድ በአንድ እንመለከታለን

1 ወንጌልን መስበክ ክርስቶስ ከትንሳኤው ቦኃላ እና ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርት ያስተማራቸው "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃቸዋቸው ያዘዝኳቸሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራቸዋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።

እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፊጻሜ ድረስ ከናንተ ጋር ነኝ" አላቸው (ማቴዎስ 28፡19~20) በሌላ ቦታም " ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" አላቸው (ማርቆስ 16፡15~16) በኃላ ላይም ጳውሎስ ወጣቱን አገልጋይ ሲመክር "ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርክ ዝለፍና ገስጽ ምከርም" አለው (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡2) በነዚህ ጉዳዮች ብዙ ጥቅሶች ቢኖሩም የጌታን ፈቃድ ለማሳዬት ለጊዜው በቂ ነው፡፡

በሓዋርያት ዘመን ቤተክርስቲያን ምን ታደርግ ነበር? አባላቶቿ ጌታ የጠየቃቸውን ያደርጉ ነበር፡፡ የጌታን ቃል ይሰብኩ ነበር፡፡የሃዋርያት ሥራ መጽሃፍ በዚህ የተሞላ ነው፡፡ ለምሳሌ ሓዋርያት ምዕራፍ 2፤ ምዕራፍ 8፤ ምዕራፍ 9፤ ምዕራፍ 10፤ ምዕራፍ 16 ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ነገር ግን ማስተማሩንና መስበኩን እነማን ናቸው ሲያደርጉ የነበሩት? በጌታ ህዝብ ላይ በኢዬሩሳለም ታላቅ ስደት በተፈጸመበት ጊዜ ተመዝግቦ የሚናነበው "የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ" የሚል ነው፡፡ (የሓዋርያት ሥራ 8፡ 4)፡፡

ቀጥሎ፣ ምንድነው የሰበኩት? እንዷገና ማድረግ ያለብህ ነገር የሓዋርያት ሥራ መጽሃፍ ውስጥ ያሉትን የእምነት ጉዳዮች ማንበብ ብቻ ነው እና አንተም ለራስህ አጥናው፡፡ ነገር ኝ ባጭሩ የክርስቶስን አምላክነት ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለብን የቤተክርስቲያንን አስፈላጊነት የአምልኮን ሁኔታ የክርስቲና ህይወት አስፈላጊነትና ወዘተ ይሰብኩ ነበር፡፡ ጳውሎስ ይህን ሲገልጽ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሄር ኃይል ነው" ብሏል፡፡ (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18)

ጳውሎስ ቃሉ እንዲሰበክ ጌታ ካዘዘው ከመናገሩም በተጨማሪ እምነት የሚመጣው ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሄር ቃል ነው ብሏል፡፡ (ሮሜ 10፡17) ክርስቶስም "እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣቸዋል" ብሏል (ዮሃንስ 8፡32)ቀጥሎ "እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙጽ እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? " ይላል (ሮሜ 10፡14) እነዚ ሁሉ ሰው በአጥያት መጥፋቱን ለማሳዬት ነው፡፡ (ሮሜ 3፡23፣ ሮሜ 6፡23) ሲለዚህ የእግዚአብሄርን ፍቅር የሆነሁን ወንጌልን መስበክ ያስፈልጋል (ዮሃንስ 3፡16) ስለዚህ ሰውየእግዚአብሄር ቃል በመታዘዝ ከኃጥያቱ ሊድን ይቸላል (ሮሜ 1፡16~17፣ ማርቆስ 16፡15.16) እነዚህን የእግዛብሄርን ቃል የጣሉና የማይታዘዙት ሁሉ ይጠፋሉ (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7`9) ስለዚህ ይህ የእግዚአብሄር ወንጌል ሊሰበክ ይገባል፡፡

2 ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድሆችን መርዳት በጌታ ቃል ውስጥ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዷሚያስቡ እና እንዷረዷቸው

የሚያስችል መንገድ እንዳለ የሚያሳዩ ምሳሌዎች አሉን በሐዋርያት ሥራ 2፡45 ላይ “ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ መሬታቸውንም ጥሪታቸውንም እየሸጡ ማንኛውም እንደሚያስፈልጋቸው ለሁሉ ያካፍሉ ነበር። ነገር ግ ን በሃዋርያት ሥራ 6 ላይ በግሪክ ሰዎችና በዕብራዊያን መካከል ስለተፈጠረ አለመግባባት እናነባለን ምክ ያቱም ዕብራዊያን መበለቶች በዕለት ዕለት አገልግሎት ቸላ ተብለዋል። ስለዚህ ሐዋርያቱ ደቀመዛሙርቱን ሰብስበው ይህንን የቤተክርስቲያን ሥራ እንዲሠሩ እንዲሾሙ ከመካከላቸው ሰባት ሰዎችን እንዲመርጡ አደረጉ።

ስለጳውሎስም የምናነበው በእዬሩሳሌም ያሉትን ቅዱሳን ድሆችን ለመርዳት እንደሄደ ስናነብ እንዲህ ይላል “አሁን ግ ን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ እየሩሳሌም እሄዳለሁ። መቄዶኒያና አካይያ በእዬሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወድዋልና” (ሮሜ 15፡ 25~26) እናም ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ወንድሞች ሲጽፍ “ ለቅዱሳንም ገንዘብን ለማዋጣት በገላቲያ አብያትክርስቲያናት እንደደነገግኩ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት ያንጊዜ እንዳይሆን ከናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያቀለ በቤቱ ያስቀምጥ” (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2)።

ማን ነው ሊረዳ የሚያስፈልገው? እንደሚታወቀው በቅድሚያ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ነው። እነሱም ድሆች፤ በዕድሜ የገፉና ራሳቸውን መርዳት የማትችሉ፤ መበለቶች አስቸኳይ እርዳታ ፈላጊ፤ ወላጅ አልባ ህጻናት ክርስቲያኖች ወዘተ እነሱ ብቻም ሳይሆን “እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለስው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ (ገላትያ 6፡10)፣ በጢሞቴዎስ 5 ላይ አንድ ሰው ሊረዳ የሚገባው ራሱን ወይም ራሷን መርዳት በማይችሉበት ጊዜ የሚረዳ ዘመድ የሌለው ብቻ እንደሆነ እና ይህ ሰው ታማኝ ክርስቲያን መሆኑ የተመሰከረለት ብቻ ነው። ስለዚህ የጌታን ገንዘብ ለሚለምነው ሁሉ ሳይሆን ለሚገባቸው ብቻ መዋል አለበጥ

የቤተክርስቲያን አባላት ብቻ ሳይሆን ደካማ ለሆኑ በውጭ ላሉትም የሚረዳበት ሁኔታ አለ። ያዕቆብ 1፡27፣ እና ያዕቆብ ምዕራፍ 2ን አንብብ። ይሄ ማለት ህብረተሰቡን ከወንጌል ጋር መድረስም ይሆናል ማለት ነው።

ነገር ግን ለዚህ የሚውል ገንዘብ ከዬት ይመጣል? እንሂህ ገንዘቦች ወይም ፈንዶች የሚመጡት ከቤተክርስቲያን አባላት ነው። ይህም በልባቸው ያሰቡትን ሲሰጡ ነው( 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 9፡7) ይህ ማለት ቤተክርስትያን የማትሰጥ ከሆነ የተቸገሩትን መርዳት አይቻልም ማለት ነው።

3 ቤተክርስቲያንን ማነጽ፡~ ማነጽ ማለት ማጠናከር፣ማበረታታት፣ የቤተክርስቲያን አባላት በመንፈሳዊ እንዲያድጉ መረዳት ማለት

ነው፡፡አንዳንድ የሚያንጹ ነገሮች ምንድናቸው? የእግዚአብሔር ቃል ህብረት፣በአምልኮ መካፈል፣መረዳዳት፣መልካም ሥራ፣ፍቅር ወዘተ፡፡ ይህንን ሊያስረዱ የሚችሉትን እነዚህን አንብባቸው፡፡ ሐዋሪያት ሥራ 9፡31, ሮሜ 14፡19, 1ኛ ቆሮንቶስ 8፡1, 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡11, 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡26,2ኛ ቆሮንቶስ 12፡19 እና ኤፌሶን 4፡12ን ጊዜ ወስደህ አንብብ፡፡

በአጠቃላይ ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያን ያለ አለም አቀፍ ድርጅት፣አንድ ሰው ልዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ነገር ሳይኖር እንዴት እነዚህን ነገሮች ማድረግ ትችላለች ብለው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን የጌታ መንገድ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ነው፡፡ እሱ ሥራውን ለመስራት አንድና ብቸኛ መንገድ ነው እግዚአንሔር ሊመሰገን ሊከበር እና ሊከብር የሚችለው ፍቃዱን ስናደርግ በዚህ የመሆንን ዓላማ ስንፈጽም ብቻ ነው፡፡ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው እና እያንዳንዱ መ ምዕመናን እንዲሁም እያንዳንዱ አባል የድርሻውን መወጣት አለበት ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሥራዋን መሥራት የምትችለው መ ምዕመናን የአቅማቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡

ወንጌልን መስበክ፣የተቸገሩትን መርዳት፣ቤተክርስቲያንን ማነጽ ሁሉም የሰውን ነፍስ ለማዳንና በመጨረሻም እግዚአብሔር በእነዚህ ሁሉ እንዲመሰገን ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ከእነዚህ ሦስቱ በቀር ሥራ የላትም ፖለቲካ ንግድና ቤተክርስቲያንን ወደ ማህበራዊ ድርጅትነት መለወጥ ለእግዚአብሔር ቃል እንግዳ ናቸው፡፡ የጌታ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አካል ነች፡፡በዓለም ውስጥ ናት ዱሩ ግን ከአለም አይደለችም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እና ሰውን ለማገልገል ንጹህ ቅድስናን ለመጠበቅ የአባላቱን መዳን እና የፈጣሪን ክብር ለማስገኘት ይቺን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሥራዋንና ተልኮዋን ነው፡፡

## ጥያቄዎች
## ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1 የጌታ ቤተክርስቲያን በምን ጉዳይ ላይ ነው የምሠራው

2. የሃይማኖቱ ዓለም ለጥቅም ሲባል በተለያየ የንግድ ዓይነቶች በመሰማራቱ ጥፋተኛ ነው?

3. የቤተክርስቲያን ሥራዎች ምን ምንድናቸው?

4. በማቴዎስ ወንጌል 28፡19~20 እና በማርቆስ ወንጌል 16፡16 ላይ የጌታን ተዕዛዝ ጥቀስ

5. የጥንቷ ክርስቲያኖች በተሰደዱበት ጊዜ ምን እንዳደረጉ ተናገር

6. በዚያን ጊዜ የሰበኩት ምን ነበር?

7. እምነት እንዴት ይመጣል?

8. ነጻ የሚያወጣው ምንድነው?

9. አንድ ሰው እንዴት ሊድን ይችላል?
10. የሚጠፉት እነማን ናቸው?
11. እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቤተክርስቲያን ይመለከታታል?
12. በእየሩሳሌም ለድሆች የሚያስፈልገውን ያዋጡት እነማን ናቸው?
13. ሁሉንም ሰዎች መርዳት ይገባል?
14. በቅድሚያ ሊደገፉ የሚገባቸው እነማን ናቸው?
15. የድጋፍን ገደብ ጥቀስ
16. ከቤተክርስቲያን ውጭ የሆኑትን የበለጠ መደገፍ ይገባል?
17. እነዚህን ለመርዳት ፈንድ ከዬት ይመጣል?
18. ይህ ፈንድ ማዋጣት የሚገባ መቼ ነው?
19. ማነጽ የሚለውን ቃል ዘርዝር
20. አንዳንድ የሚያንጹ ነገሮች ምንድናቸው?
21. እግዚአብሄር እንዴት ሊመሰገን ሊከብር ሊከበር ይችላል?
22. የኤተክርስቲያን ራስ ማን ነው?
23. የቤተክርቲያን ሥራ ዓላማ ምንድነው?
24 ቤተክርስቲያን ከዓለም ናት?
25 ፖለቲካ ንግድ ወዘተ ለቤተክርስቲያን እንግዳ ናቸው?

## ትምህርት አሥር
## የቤተክርስቲያን ሥራ

የሃይማኖቱ ዓለም ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በላይ የቤተክርስቲያን አንድነት ያሳሰበው ይመስላል፡፡ በየቦታው የስውን ምናብ የሳበው እንቅስቃሴ ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በዓለም ላይ ብዙ ሃይማኖታዊ ክፍፍል ስላለ ነው፡፡ እና ሁሉም ስለሰለቹ ነው፡፡ ሆኖም ግን የሰዎች የሃይማኖት አካላት ላለመስማማት ሲስማሙ አንድነትን በፊጹም ማምጣት አይቻልም፡፡ የተወሰነ ደረጃ ህብረት ወይም ስምምነት ሊኖር ቢችልም ክፍፍሉ አሁንም ይኖራል፡፡ ታዲያ መልሱ ምንድነው? መልሱ በራሱ መጽሃፍ ቅዱስ ላይ ነው፡፡ እውነተኛ አንድነት እንዲኖር ሰዎች ትምህርታቸውን፣ ስማቸውን፣ ቤተክርስቲያናቸውን፣ የሃይማኖት መግለጫ መጻህፍታቸውን ትተው መጽሃፍ ቅዱስን ብቻ አንብበው አጥንተው አምነው እና ሲታዘዙ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሲሆን በዮሃንስ ወንጌል 17 ላይ ጌታ እንደጸለየው ዓይነት እውነትኛ አንድነት ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዎች ይህን ሲያደርጉ ሁሉም አንድ ስም ይለብሳሉ፣ ሁሉም አብረው ይሠራሉ፣ ሁሉማንድ ነዶርያምናሉ፣ ሁሉም ለአንድ ትምህርት ይታዘዛሉ፣ ሁሉን አንድ ዓይነት ትምህርት ያስተምትራሉ፣ ሁሉም በአንድነት ወደ

ሰማይ ይሄዳሉ። ሰው ሰውን መከተል ትቶ ክርስትቶስን መከተል ሲጀምር አንድነት እንዲኖር ቀላል ይሆናል።

ቅዱሳት መጽሃፍት መከፋፈልን ያወግዛል። መጽሃፍ ቅዱስ እግዚአብሄር በወንድማማች መካከል መልያየትን ወይም ጠብን የሚዘራውን ይጠላል ይላል (ምሳሌ 6፡10)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 1 ላይ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን መከፋፈሏ ተነግሮናል። ሃዋርያው ጳውሎስ እነዚህን መሰል ነገሮችህ ከማመስገን ይልቅ የችግሩን መንስኤ ለማጥፋት ወዲያሁኑ እርምጃ ወስዷል። እንዲህ ይላል “ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና ሃሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችዋለው” ( 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10)። ቀጥሎ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ሦስት ጥያቄዎችን ይጠይቃቸዋል ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስ ለናንተ ተሰቅሏልን? በጳውሎስ ስም ተጠምቃችዋል? ብሎ ሲተይቃቸው መልሳቸው አሉታዊ ሆኖ ለሁሉም ጥያቄዎች መልሳቸው አይደለም ነው። ይህንን በማለት የተከፋፈሉበትን ሁኔታ በሞኝነት መሆኑን አሳይቷል።

ይሄው ሃዋርያ ጳውሎስ ሮሜ ላሉት ወንድሞችህ ሲጽፍ “ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችዋለሁ። ከነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ። እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆሳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና። በመልካም በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሊለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ” (ሮሜ 16፡17~18) እንደዚሁም ለቆላስያስ ሲጽፍ “ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ እንደሰው ሥራዓትና ትምህርት አትያዝ አትቅመስ አትንካ ለማለት ትዕዛዝ በዓለም እንደምትኖሩ ስለምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ ሊጠፉ ተወስነዋልና” (ቆላስያስ 2፡20~22) ከማቴዎስ 15፡9፣ ጋር አስተያይ

ይህ ሁሉ የስውን ትምህርት ትምህርት ትዕዛዛትን ሰዎችን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከመጽሃፍ ቅዱስ ውጪ ሌሎች መጽሃፍትን መቀበልና መከተል መለያየትን የሚፈጥሩ ናቸው ለማለት ነው። በሌላ በኩል አንድነት ሊኖርና በሱ ልኮን የሚቻለው ክርስቶስን ሲከተሉ ብቻ ነው። ምክን ያቱም ክርስቶስ ስለ አንድነት እንድህ ብሎ ጽልዮአልና “ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ከቃላቸው የተነሳ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለነዚህ ብቻ አልለምንም። አንተ እንደላከከኝ ዓለም ያምን ዘንድ አንተ አባት ሆይ በኔ እንዳለህ እኔም ባንተ እነርሱ ደግሞ በኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ” (ዮሃንስ 17፡20~21) አሁን ክርስቶስ ስለማይቻል ነው የጸለየው? አይደለም በርግጥ ሊሆን ለሚችል ጉዳይ ነው የጸለየው። መቼ? ክርስቶስን ሲከተሉት አንድነት ይቻላል። ሰው ሰራሽ ትምህርት

ይከፋፍላል የመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት ግ ን አንድ ያደርገናል።

በኤፌሶን 4፡1~6 የአንድነትን ፎርሙላ እናነባለን እንድህ ይላል በደንብ አስትውል “እንግድህ በጌታ እስር የሆንኩ እኔ በተጠራችሁበት እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችዋለው በትህትና ሁሉና በየዋህነት በተዕግስትም እርስበርሳችሁ በፍቅር ታገሱ በሠላም ማሰርያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ የመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ትምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ” (ኤፌሶን 4፡1~6) አስተውል ይህ ስለአንድነት ነው፡፡ በደንብ አስተውል በያንዳንዱ በተመዘገቡት ውስጥ የሚናገረው ስለአንድነት ነው፡፡ እስቲ እነዚህ ውስት ከአንድ በላይ የሚገልጽ ሃሳብ ያገኘ አለ?

የአንድነትን ስሜት የምናየው ክርስቶስ ቤተክርስቲያኔን እሰራለው ሲል ነው፡፡(ማቴዎስ 16፡18)ይህ ማለት አንዲት ቤተክርስቲያን ማለት ነው፡፡ይህ ማለት የእሱ አንድ አካል ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡27)እሱ ራስ የሆናት ማለት ነው፡፡(ቆላስያስ 1፡18) በእርግጠኝነት ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ራስም ነው፡፡ብሎ የሚከስ አይኖርም፡፡ቤተክርስቲያን የእግዚአብሄርቤትወይምየእግዚአብሔርቤተሰብተብሏል(ጢሞቴዎስ 3፡15) ነገር ግን ስንት ቤቶች ወይም ስንት ቤተሰብ ናቸው?አንድ ሌላ የእግዚአብሔር መንግስት የክርስቶስ መንግስትን እናነባለን፡፡(ዮሐንስ 3፡3~5፤ቆላስያስ 4፡11፤1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡15) ስንት መንግስቶች ነው ጌታ ያለው ስንት ንጉሶችስ ናቸው የሚኖሩት በትክክል አንድ ንጉስ እና አንድ መንግስት ነው፡፡

ወደፊት ጠልቀን ስናየው በርግት መጽሐፍ ቅዱስ የሐይማኖት ድርጅቶችን የመለየየትን አስተሳሰብ ይቃወማል፡፡በሌላ በኩል መጽሐፍ ቅዱስ አንድነትን ያሳያል፡፡ሙሉነትና ሙሉነትን ነው፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን እምነታቸውን እና ልምዳቸውን ምንም ይሁን ምን በሁሉም ሃይማኖታዊ ሰዎች የተዋቀረች ሚስጥራዊ አካል መሆኗን ባይገልጽም የተጠሩት ክርስቶስን የተከተሊና የታዘዙትን ያቀፋችሁ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗን ያሳያል፡፡ትምህርቱ ክርስቶስ አልተከፋፈለም ቤተክርስቲያንም አልተከፋፈለም በማንኛውም መንገድ መከፋፈል ወይም መለያየትን መደገፍ ክርስቶስን እና የጸለየውን ጸሎት መቃወም ነው፡፡

ጥያቄዎች

ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ዛሬ ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት ልመና አለ ወይ?

2. አንድነት ብዙ የተፈለገበት ምክንያት ምንድነው?
3. የሃይማኖት አካላት ላለመስማማት ሲስማሙ አንድነት ማምጣት ይቻል ይሆን?
4. በአንድነት ጥያቄ መልሱ ምንድነው?
5. በአንድነት እንዲኖር ሰዎች ምን መተው አለባቸው?
6. ሁላችንም አንድ እንድንሆን ማነው የጸለየው?
7. የአንድነት ውጤት ምን ሊሆን ይችላል?
8. መጽሐፍ ቅዱስ መከፋፈልን ያወግዛል?
9. እግዚአብሔር የሚጠላው ማንን ነው?
10. 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10 ግለጽ
11. ጳውሎስ የቆሮቶስ ቤተክርስቲያንን የጠየቃቸውን ሦስቱን ጥያቄዎችን ጥቀስ
12. ምን ዓይነት የሰዎች ቡድን ምልክት ሊደረግበት ይገባል?
13. ማንን ያገለግላሉ?
14. ከነሱ መራቅ አለብን?
15. ጌታን በከንቱ የሚያመልኩት እነማን ናቸው?
16. ክርስቶስ የጸለየው በምን ጉዳይ ላይ ነው?
17. ክርስቶስ ለማይቻል ነገር ነው የጸለየው?
18. የአንድነትን ፎርሙላ ጥቀስ
19. እዚያ ውስጥ ስንት አንዶች አሉ?
20. ክርስቶስ ስንት ቤተክርስቲያን ነው የመሰረተው?
21. ቤተክርስቲያን ምንድነው?
22. የቤተክርስቲያን ራስ ማን ነው?
23. ክርስቶስ ከአንድ አካል በላይ ወይም ካንድ ራስ በላይ አሉት?
24. ጌታ ስንት ቤተሰብ አሉት?
25. የእግዚአብሄር ቃል ይከፋፍላል ወይስ አንድ ያደርጋል?

## ትምህርት አስራ አንድ
## የቤተክርስቲያን ክሪድ

ይህ የቤተክርስቲያን ክሪድ የሚለው (creed) የሚል ሲሆን ቃሉ የመጣው ከላቲን ነው፡፡ የ ሃይማኖታዊ እምነት ፎርሙላ ማንኛውም የሃይማኖት ቀመሮች ወይም ኑዛዜ መርሆች ወይም አስተያየቶች ማጠቃለያ ተብሎ ይገለጻል፡፡ የሃይማኖት መግለጫው ዘወትር የሚያስበው “የሃዋርያት እምነት” እና መልካሙ የእምነት መግለጫ ቢሆንም አንዱም በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም፡፡ ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ሃይማኖት እምነት የሠራው የመሰረተው የራሱ ሰው አለው ይህም የሃይማኖቱ መግለጫ በመመሪያ በሥራዓት በትምህርት በእምነት

መናዘዝ ወዘተ ነው። ሁሉም በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተጨማሪዎች ናቸው።

ዬትኛውም የሃይማኖት መግለጫ መጽሃፍ ከመተን በላይ እንዲያዘ ሊመከር ይችላል። ከመጽሃፍ ቅዱስ ያነሰ የያዘው በጣም ጥቂት ነው። ከመጽሃፍ ቅዱስ ተጨምሮበትም ቢሆን እሱም ከንቱ ነው።ምክን ያቱም ቀድሞ መጽሃፍ ቅዱስ አለን። ዮሃንስ ራዕይ 22፡18፣ 19፣ ገላቲያ 1 ፡6<sub>፟</sub> በእግዚአብሄር ቃል ላይ መጨመር እንዲሌለብን ከቃሉ መቀነስ እንዲሌለብን በቃሉ ላይ መተካት እንዲሌለብን አበክሮ ይናገራል። በሌላ አነጋገር ቅዱሳት መጽሃፍት የተሟሉ ናቸው (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17) ፊጹማን ናቸው (ያዕቆብ 1፡25) እና እኛ ልንናገር የሚገባን እንደእግዚአብሄር ቃል መሆን አለበት (1 ጴጥሮስ 4፡11) ስለዚህ ተጨማሪ መጽሃፍ ወይም ተጨማሪ ጽሁፍ አያስፈልገንም።

በዚህ ዘመን ሃይማኖታዊው ዓለም የተከፋፈለው ህዝቡ የእግዚአብሄርን ቃል ስለተከተሉ ሳይሆን የሰዎችን ክሪድ (እምነት) ስለተቀበሉ ነው። ይህ ደግሞ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የራሱ የሆነ የሥርዓት ስብስብ ወዘተ አለው። ምን ያህል እንደሚያሳዝን። ስለዚህ የኛ ልመና አንድ እና ሁሉም ሰው ሰራሽ የሆኑትን መጽሃፋቸውን አጥፍተው ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ብቻ እንዲመለሱ ነው። እርሱም የእግዚአብሄር ቃል ነው። እርሱ በክርስቶስ እየሱስ አንድ ያደርገናል እንጂ አይከፋፍለንም።

የጌታ ቤተክርስቲያን ክሪድ (እምነት) ምንድነው? እኛ ሌላ አዳኝ የለንም ክርስቶስ ብቻ ነው እንጂ። ሌላ ክሪድ (እምነት) የለንም መጽሃፍ ቅዱስ ብቻ ነው እንጂ። በሃማኖት ውስጥ ያለን አስተያየቶች እና ሃሳቦች ዋጋ ቢስ ናቸው። የመጽሃፍ ቅዱስ የግል ትርጉም የለንም ያለን ሁሉ መጽሃፍ ቅዱስ ነው። ትምህርቱን ታዘናል ሌሎችንም እንተቁማለን ልመናችን አንድ ነው አንብበን እንድናተናው ነው። (ዮሃንስ 5፡39፣ 2 ጢሞቴዎስ 2፡15) እናም ሰዎች መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ዬትም እንዲያደርጉ እንጠይቃለን።

ተጨማሪ መጽሃፍ የለንም ወይም ሌላ የምንከተለው መጽሃፍ የለንም። መጽሃፍ ቅዱስን የሚስተካከል የህግና የሥርዓት መጽሃፍ ሊጽፍ የሚችል ሰው ይኖራል ብለን አናምንም። ጌታ ለማንም ሰው እንዲዚህ ዓይነት መጽሃፍ እንዲጽፍ መብት ሰጥቷል ብለን አናምንም። ይህን መጽሃፍ እንዲጽፍ መንፈስ ቅዱስ ማንንም አነሳስቷል ብለን አናምንም።

የእግዚአብሄር ቃልና የእግዚአብሄር ቃል ብቻ ነው ከእግዚአብሄር በመንፈሱ መሪነት የመጣልን። ሊያድነን የሚችልም እሱ ብቻ ነው መጽሃፍ ቅዱስ በተጨማሪም በመጨረሻው ቀን ሊፈርድብን የሚችል በዚሁ ቃል መሰረት ብቻ ነው።(ዮሃንስ 12፡48) ለነዚህና ለሎችም ምክን ያቶች ብቸኛ መመሪያችን አድርገን የምንቀበለው መጽሃፍ ቅዱስ ብቻ

ሲሆን ሌሎችንም እንደዚህ እንዲያደርጉ እናበረታታለን።

እውነትን ለመማር ወደ መጽሃፍ ቅዱስ እኼዳለን እሱ እውነት እስከሆነ ድረስ (ዮሃንስ 17፡17፣ ዮሃንስ 8፡32) ወደ እውነት ምንጭ እስካልሄድክ ድረስ እውነትን ልታገኝ አትችልም። ስለዚህ እውነትን ለማመን እውነትን መስማት አለብህ (ሮሜ 10፡17) ብዙዎቸ ሰዎቸ በሃይማኖት ጉዳይ መታለላቸው አያስደንቅም። በሃይማኖቱ ዓለም መከፋፈልና ግራ መጋባት መኖሩ አያስደንቅም። ሰዎቸ እርዳታ ለማግኘት ወደ መጽሃፍ ቅዱስ እንደመሄድ ወደ ሰዎቸ ይሄዳሉ። ሰዎቸ ወደ ተጻፈው መሄድ ቃል መሄድ ሲገባቸው ወደ ሰዎቸ ትምህርት ይሄዳሉ። በርግጥ ሰዎቸ የእውነት መዳን ከፈለጉ ወደ መጽሃፍ ቅዱስ መመለስ አለባቸው።

ሰዎቸ ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ተመልሰው ስለቤተክርስቲያን እውነት እንዲማሩ እናበረታታለን።ብዙ ተመሳስለው የሚታዩ አብያተክርስቲያናት በዓለም አሉ። ዬትኛው ነው ትክክለኛ? ስለ እያንዳድንዳቸው የተለየ ጥናት ማድረግ አለበት? አይደለም ስለቤተክርስቲያን እውነቱን ወደሚናገረው መጽሃፍ ቅዱስ ሰዎቸ መሄድ አለባቸው። ስለጌታ ቤተክርስቲያን እውነቱን ካወቀ በኃላ የመጽሃፍ ቅዱስን ትምህርት የሚከታተተለውን ማግኘት አይቸግረውም።

ሰዎቸ ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ሄደው ስለእውነት እንዲማሩና አንድ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲያውቁ እናበራታታለን እንደሰዎቸ አስተምሮ ብዙ የመዳን መንገዶቸ አሉ ነገር ግ ን ወደ እግዚአብሄር መጽሃፍ ስንሄድ በቀላሉ የምናገኘው ተጠቅሶ ያለው አንድ ሰው ለመዳን በመጀመሪያ መስማት አለበት፣ ማመን አለበት፣ ከኃጥያቱ ንሰሃ መግባት አለበት፣ ክርስቶስን መመስከር አለበት ለኃጥያቱ ስርየት መጠመቅ አለበት (ማርቆስ 16፡15~16፣ ሓዋርያ ሥራ 2፡38) ክርስቶስ ብቻ አዳኝ ነው። እና አንድ ሰው ቃሉን ሰምቶ ለመዳን መታዘዝ አለበት

ሰዎቸ ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ሄደው እንዴት እንደሚመለክ እንዲያጠኑ እናበረታታቸዋለን። በበተቃራኒው ሰዎቸ ለማምለክ ብዙ የተለያየ መንገድ እንዳለ ቢናገሩም እና ቢያደርጉም መጽሃፍ ቅዱስ ጌታን የምናመልክበት አንድ መንገድ ያስተምረናል (ዮሃንስ 4፡24)።

በነዚህ ነጥቦቸ ላይ ብቻ ሳይሆን ስለደህንነት እና ህይወት እና መልካምነት በሚመለከቱ ሁሉም ነጥቦቸ ላይ እውነቱን ለማየት ወደ መጽሃፍ ቅዱስ እንዲሄዱ እናበረታታለን። ሰው ግ ን መጽሃፍ ቅዱስ መረዳት የማይቻል አድርገው ይተውታል ይህ ግ ን ትክክል አይደለም። ዲያብሎስ ሰዎቸ እንዲጠፉ ስለሚፈልግ ከመጽሃፍ ቅዱስ እንዲርቁ ያደርጋል። ለመዳን ግ ን ሰዎቸ ወደ መጽሃፍ ቅዱስ በመሄድ ማመን እና በዚህ ጉዳይ ብቸኛ መመሪያ አድርገው ሊቀበሉ ይገባል።ይህንን ሲያደርግ ብቻ ነው ሰው የሚድነው ምክን ያቱም ያኔ ብቻ ነው ከትክክለኛው ጋር

የሚገናኘው፡፡

የእኛ እምነት ምንድነው? ኢየሱስ ክርስቶስ እና ቃሉ በቀር ሌላ የለም፡፡ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እና ቃሉም የመጭረሻ እንደሆነ እናምናለን፡፡ እሱን ብቻ ተቀብለን እንከተላለን ሌሎችንም እንድሁ እንዲያደርጉ እናሳስባለን እናበረታታለን፡፡ የሰዎች እምነት ወደ አንድ ቦታ ይወስዳል ወደ ገሃነም ይመራል፡፡ ኢየሱስ ግ ን ወደ መንግስተ ሰማያት ይመራል " እኔ መንገድ እውነትና ህይወት ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ ማንም የለም" ብሏል (ዮሃንስ 14፡6)

## ጥያቄዎች
## ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ክሪድ የሚለውን ቃል አብራራ
2. እያንዳንዱ ሰው ሰራሽ ሃይማኖት ምን አለው?
3. በመጽሃፍ ቅዱስ ቃል ላይ የሚጨምሩት በሚቀንሱት ላይ ምን እንደሚከሰት ተናገር
4. መጽሃፍ ቅዱስ የተሟላ ነው?
5. ፊጹም የሆነው ምንድነው?
6. እንደት ነው መናገር መስበክ ያለብን?
7. ሌላ ተጨማሪ መጽሃፍ ያስፈልጋል?
8. የሃይማኖት ዓለሙ ዛሬ የተከፋፈለው ለምንድነው?
9. መጽሃፍ ቅዱስ ይከፋፍለናል?
10. የጌታ ቤተክርስቲያን ክሪድ ምንድነው?
11. የኛ የግል አስተያየትና ሃሳብ በቃሉ ላይ ዋጋ አለው?
12. በግላችን በመጽሃፍ ቅዱስ የራሳችን ትርጉም የመስጠት መብት አለን?
13. መጽሃፍን የምስተካከል መጻፍ የሚችል ሰው አለ?
14. ጌታ ለሰዎች መጽሃፍ ቅዱስን የሚስተካከል እንዲጽፉ መብት ሰጥቷል?
15. የእግዚአብሄር ቃል የመጣው ከዬት ነው?
16. በመጨረሻው ቀን የሚፈርድብን የትኛው ቃል ነው?
17. እውነት ምንድነው?
18. ሰው ለእርዳታ መሄድ ያለበት ወደ ማን ነው?
19. ስለቤተክርስቲያን እውነታ ለመማር ወደ ዬትኛው መጽሃፍ መሄድ አለብን?
20. ብዙ የመዳን መንገዶች አሉ?
21. አንድ ሰው ለመዳን ማድረግ ያለበትን መጽሃፍ ምን ያስተምራል?

22. በአምልኮ ጊዜ ማድረግ ያለብንን ጌታ ገልጦልናል?
23. መጽሃፍ ቅዱስን መረዳት ይቻላል?
24. በተመሳሳይ ሁላችንም መረዳት እንችላለን?
25. ብቸኛው ወደ አብ የሚወስድ መንገድ ማን ነው?

## ትምህርት አሥራ ሁለት
## የቤተክርስቲያን ታሪክ

በሓዋርያት ምዕራፍ 2 የቤተክርስቲያን ወይም የእግዚአብሄር መንግሥት ምስረታ ነበር። ሓዋርያት በ ኢየሩሣሌም ነበሩ። መንፈስም በእነሱ ላይ ፈሰሰ። ለበዓለ ሃምሣ ቀንብዙ አህዛብን ወክለው ሰዎች ተሰብስበው ነበር።ጴጥሮስና ሌሎች ሃዋርያት ይህ በነብዩ ኢዩኤል የተነገረው ትንቢት ፊጻሜ መሆኑን አውጇዋል። ክርስቶስ ሞቷል ስለዚህም የመጨረሻው ዘመን ተጀመረ ንሠሃ እና የኃጥያት ስርዬት ተሰበከ 3000 የሚያህሉ ነፍሳት የወንጌልን ስብከት ሰምተው ተጠመቁ። ጌታም ወደ ቤተክርስቲያን ጨምሮአቸዋል። ከዚያም ወንጌል ከኢየሩሳሌም እስከ ይሁዳ ድረስ እስከ ሰማሪያ በመጨረሻም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ከሰማይ በታች ያለው ፍጥረት ሁሉ እስኪሰማው ድረስ።(የሓዋርያት ሥራ 1፡8፤ ማቴዎስ 28፡19~20፤ ማርቆስ 16፡15~16፤ ቆላስያስ 1፡23)

በዘመነ ሓዋርያት ቤተክርስቲያን ተስፋፍታለች ወንጌል በፍጥነት ተሰራጭቷል ጳውሎስ ከተለወጠ በኃላ ለአይሁድ ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ለአህዛብም ሦስት ጊዜ ሚስዮናዊ ጉዞ አድርጓል። በውጤቱም ብዙ አማኞች ተገኝተዋል እናም በመላው ኤሺያና አውሮፓ የጌታ ቤተክርስቲያን ጉባኤዎች ተተክለዋል። ነገር ግን ብዙ ስደት ስለነበረ ይህ ቀላል አልነበረም። የመጀመሪያው ስደት የተጀመረው ከኢየሩሳሌም ነው። በዚህ ስደት ምክንያት ደቂመዛሙርት ተበተኑ። በተበታተኑበትም ወንጌልን እየሰበኩ ይዞሩ ነበር (ሓዋርያት ሥራ 8፡1~4) በጊዜው ሮማዊያን ለብዙዎች ችግሮች ክርስቲያኖችን ተጠያቂ በማድረግ በሮም እና በሮማዊያን ዓለም ውስጥ ባሉ መድረኮቻቸው ይቀልዱባቸው ነበር። ጳውሎስ በመጨረሻ ታስሮ ለፍርድ ወደ ሮም ተወሰደ። የዓለም ታሪክ እንደሚነግረን ከዮሃንስ በቀር ሓዋርያት ሁሉ በሰማዕትነት የተገደሉት ስለክርስቶስ ነው። በመቶ ሺዎች ምናልባትም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችም ህይወታቸውን አጥተዋል።

ስደት ቢኖርም ቤተክርስቲያን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሄደ። በቤተክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰው ስደት ሳይሆን በቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረ ችግር ነበር። ሓዋርያው ጳውሎስ ውድቀት ስለሚኖርበት ቀን ተናግሯል በሌላ አነጋገር ብዙዎቹ የጌታ

ቤተክርስቲያን አባላት ወደ ስህተት የሚገቡበት ቀን ይመጣል እያለ ነበር። እሱ የሚለውን እናስተውል “ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ስለጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለመሰብሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል ወይም በእኛ እንደሚመጣ በመልዕክት የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ከአዕምሯችሁ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እለምናችዋለን ማንም የማናቸውም መንገድ አያስታቸሁ ክህደቱ ሳይመጣና የዓመጽ ሰው እሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደለምና። እኔ እግዚአብሄር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሄር ቤተመቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለው ሁሉ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው። ገና ከናንተ ጋር ሳለሁ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁም? በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ የዓመፅ ምስጥር አሁን ይሠራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው አመትፀኛ ይገለጣል። ይድኑ ዘንድ የእውነት ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ የራሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሃሰተኞች ዲንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደሰይጣን አሰራር ነው። ስለዚህም ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሃሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሄር የስህተትን አሠራር ይልክባቸዋል። (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1~12) ጳኡሎስ የሚለው ይህ ነገር በዚያን ጊዜም በመካከላቸው እየሠራ እንደነበር ይናገራል። ቀትሎም እንዲህ ይላል “መንፈስ ግን በግልፅ በኃለኛው ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ በገዛ ህሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው እነዝህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ አምነውም እውነትን የማያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሄር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዛሉ” ( 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1~3) ስለ ኤፌሶን ሰዎችም ሲናገር “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችው ተጠንቀቁ ከሄድኩ ቦኃላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባቸው ደቀመዛሙርትንም ወደኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላቸው እንዲነሱ እኔ አውቃለሁና” ይላል (ሓዋርያት ሥራ 20፡28~31)።

ጳውሎስ እንዳስጠነቀቀው ከቤተክርስቲያን ተነስተው ብዙ የክርስቶስን ተከታዮችን ያስወጡ የነበሩ ሰዎች ነበሩ። መውደቁ የጀመረው በቤተክርስቲያኑ መንግስት ላይ በማጥቃት እንደሆነ ታሪክ ይነግረናል። የጌታ እቅድ እያንዳንዱ ጉባኤ የየራሱ ሽማግሌዎችና

ዲያቆናት እንዲኖራቸውና ከሌሎቹ ግን ነፃ ወይንም ጥገኛ እንዳይሆኑ ነው። ነገር ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ብዙዎቹ ጉባኤዎቹ አንዱን ሽማግሌ ወይም ኤጵስ ቆጶስን በሌሎቹ ጉባኤዎቹ ላይ ከፍ ከፍ ማድረግ ጀመሩ እና በመጨረሻም ከንዚህ ኤጵስ ቆጶስ አንዱ ጉባኤዎቹ ላይ እንዲገዛ ፈቀዱ በመጨረሻም ዉጤቱ አንዱ በመላዋ ቤተክርስቲያን ላይ ሁሉንተናዊ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ እርግጥ ነው ይህ በአንድ ቀን የተከሰተ አይደለም። ነገር ግን በብዙ ዓመታት እና በ606 ዓ ም የመጀመሪያው የዓለም አቀፍ ጳጳስ የቤተክርስቲያን ክህነት ክፍል ሃላፊ ወይም ሪዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆነ። ዛሬ እንደምናውቀው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህን ተከትለዋል። የጌታ ቤተክርስቲያንስ ምን ሆነ? ጥቂቶቹ ምዕመናን ቀጠሉ። ምክንያቱም የእግዚአብሄር መንግስት ወይም ቤተክርስቲያን እንደምትቆምና እንደምትኖር ጌታ ቃል ገብቷልና።

የሃማኖት ዓለምን በተመለከተ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የበላይ ነበረጭ እንደእውነቱ ከሆነ ዓለምን በጣም ከመቆጣጠሩ የተነሣ የሚቀጥሉት መቶ ዓመታት የጨለማ ዘመን በመባል ይታወቅ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መጽሃፍ ቅዱስን በማንበብና ለመረዳት የሚበቁት ካህናት ብቻ እንደሆኑና መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ለሰዎች እንዲሚነግሩ በመግለፅ ተራው ህዝብ መጽሃፍ ቅዱስ እንዲያነብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው። በተፈጥሮ ይህ ማለት ለሰዎቹ እንዲያውቁ የሚፈልጉትን ብቻ ይነግሯቸዋል ማለት ነው።

በዚህ ጊዜ ውስጥ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን እንደመርጨት እና ሜካኒካል ሙዚቃ በመጠቀም ትምህርቶቹ ላይ በሮማን እና ግሪክ ካቶሊክ ተብለው ተከፈሉ። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በጉባኤዎቿ ብሥራዓቷ ላይ ብዙ ትምህርቶችን ጨመረቸ በመጨረሻ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ እና በስራዓት ተበላሽታ ስለነበር ማርቲን ሉተር የሚባል ሰው እርሱ ራሱ ካህን ነበረና ቤተክርስቲአኒቱን ለማሻሻል ፈለገ። ነገር ግን እሱን አሳገዱጥ እናም ማርቲን ትክክል ነው ብሎ ያሰበውን እና ያመነውን ለማስተማርና በተግባር ለማዋል ከቤተክርስቲያን ወጣ። ከዚህ ውስጥ የተሃድሶ እንቅስቃሴ ወይም ፕሮተስታንት የሚባል ወጣ። ከዚህም ውስጥ አሁን በዘመናችን ዘመናዊ ነው የምንለው ማለት ነው ተበራከቱ። የሉተር አካሄድ በብዙ የዓለም ክፍሎች ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ለመመለስ የተደረገው ሙከራ ቀስቅሷል ይህ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ አልተሳካላቸውም።

በ17ኛውና 18ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓና በአሜሪካ ውስጥ መለያየትና ግራ መጋባት የሰለቻቸው ቤተእምነት ነበሩ። ቀስበቀስ የገቡበትን ስህተት ትተው ወደ መጽሃፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ይመለሱ

ጀመር። ምኞታቸው አዲስ እምነት ለመምስረት ሳይሆን በቅዱሳት መጽሃ ዉስጥ ያነበቡትን ቤተክርስቲያን ለመመለስ ነበር። አደረጉትም። እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ንፁህ የአዲስ ኪዳን ክርስቲና በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ያንን የ ስህተቱን በመተው የጌታ ቤተክርስቲያን አባል እንዲሆኑ መጽሃፍ ቅዱስን ብቸኛ መመሪያቸው አድርገው ይሰሙ ነበር። ክርስቲያኖች እውነትን ለመስበክ ወደ ዓለም ሁሉ ክፍሎች እየሄዱ ነው። የቀድሞዋ የጌታ ቤተክርስቲያን በአፍሪካ በህንድ በሩሲያ በፖላንድ እና ሌሎች በርካታ ቦታዎች አሁን ይገኛሉ። ያቺ የጌታ ቤተክርስቲያን ዛሬም እንደቀድሞው ትኖራለች የመጽሃፍ ቅዱስ አንድ ቤተክርስቲያን መሆኗን ለማረጋገጥ እንዷገና ወደ ሰዎች ትምህርት መሄድ አያስፈልግም። የቤተክርስቲያን አብነት ወይም ማወቂያ ያለው መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው። ያንን ስንከተል የጌታ ቤተክርስቲያን ነን። ዘሩ የእግዚአብሄር ቃል ነው (ሉቃስ 8፡11)ይህን የእግዚአብሄርን ዘር ስንዘራ የምናመርተው በሓዋርያት ዘመን የነበረችን ክርስቲና እና ቤተክርስቲያንን ነው። የጌታ መንግስት ወይም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ለዘላለም ፀንታ እንደምትቆም እንውቃለን። ስለዚህ ከተመሰረተች ቀን ጀምሮ በአንድ ቦታ ላይ ነበረ እናም ለዘላለም ፀንቶ ይቆማል ይኖራልም። ማንም ሰው ወይም ማንም ዲያቢሎስ ለማጥፋት ኃይል የለውም። ይህቺ የጌታ ቤተክርስቲያን ናት መንግስቱም ናጥ ከመጀመሪያ እስከ ፊፃሜ ድረስ አሸናፊ ሆና በመጨረሻ በጌታ ዘንድ ትሆናለጭ አሜን

## ጥያቄዎች
## ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ዬት ቦታ ነው ስለቤተክርስቲያን ምስረታ የምናኘው?
2. በዬትኛው ከተማ ነው የተመሰረተቸው?
3. በመጀመሪያው ቀን ስንት ሰዎች ቤተክርስቲያን ላይ ተጨመሩ?
4. ወንጌል የት የት ተሰበከ?
5. ጳውሎስ ስንት የተልዕኮ ጉዞዎችን አድርጓል?
6. ጳውሎስ ለአይሁዶች ስብኮአል?
7. በጳውሎስ *ሥራ* ምክንያት ቤተክርስቲያን የተቋቋመቸው በየትኛው ሁለት አህጉራት ነው?
8. ደቀመዛሙርት በተሰደዱ ጊዜ ምን ነበር ያደርጉት?
9. የጌታን ቤተክርስቲያን ያሳደደ ማን ነው?
10. በክርስቶስ ምክንያት ስንት ሓዋርያቶች ሞተዋል?
11. በስደቱ ወቅት ቤተክርስቲያን አድጋለች?
12. ጳውሎስ በመጨረሻው ይሆናል ብሎ ያስጠነቀቀው ምን

ነበር?

13. ቤተክርስቲያንን ማጥቃት እንዴት ተጀመረ?

14. በ606 ዓ ም ምን ተፈጠረ?

15. በጌታ ቤተክርስቲያን ላይ ምን ተፈጠረ?

16. ለምንድነው የሚቀጥሉት 100 ዓመታት የጨለማ ዘመን የተባለው?

17. ካቶሊክ የተከፋፈሉበትን ሁለቱን ጥቀስ

18. ከካቶሊክ ወጥቶ በተክርስቲያንን አሻሽላለሁ ያለው ስም ጥቀስ

19. ለምን ለማሻሻል ፈለገ?

20. ከዚያ ታላቅ እንቅስቃሴ ውስጥ ምን የሚሉት ወጣ?

21. በዚያ እንቅስቃሴያቸው ተሳክቶላቸዋል?

22. በ17ኛውና 18ኛው ክፍለ ዘመን ምን ተፈጠረ?

23. እነዚህ ሰዎች ለጌታ ቤተክርስቲያን ምሳሌ ወደ መጽሃፍ ቅዱስ በመመለስ አዲስ ቤተክርስቲያን ጀመሩ?

24. በሌሎች የዓለም ክፍሎች ክርስቲያኖች ዘንድ ተመሳሳይ ቤተክርስቲያን ተገኝቷል?

25. እውነተኛው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ባሁኑ ዘመን አለ?

## ትምህርት አሥራ ሦስት
## የዛሬዋ ቤተክርስቲያን

የጌታ ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ነው (ሓዋርያት ሥራ 2)። ዛሬም ያቺ ቤተክርስቲያን እንደዚያው ጊዜ አለች "ግን ይኄ ነገር እንዴት ሊሆን ቻለ?" ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። በቀላሉ ስለቤተክርስቲያን በአዲስ ኪዳን ላይ የተጻፈውን በመከተል ብቻ ነው።

አንዳንዶች በጌታ የተቋቋመችው ቤተክርስቲያን ዛሬም ያው ቤተክርስቲያን መሆኗን ለማረጋገጥ ከዓመት እስከ ዓመት ጴንጠቆስጤ ቀን እንመለከታለን የሚል እምነት አላቸው። ሆኖም ግን ይህ እውነት አይደለም። በመጀማሪያ ደረጃ ጌታ መንግስቱ ወይም ቤተክርስቲያኑ ለዘላለም ፀንቶ እንደሚኖር ነግሮናል። ፈፅሞ አትፈርስም። (ዳኒኤል 2፡44፣ ሉቃስ 1፡33፣ ዕብራዊያን 12፡28) ይህ ማለት ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በዓለም ዙሪያ እኖራል አለም። ይህ እውነት እንደሆነ ሁልጊዜ የአዲስ ኪዳን ቃል የእግዚአብሄር ዘር (ሉቃስ 8፡11) ስንዘራ የምናገኘው ምርት በሓዋርያት ዘመን የነበሩ ዘሮችን ወይም ክርስቲያኖችን ነው። እውነተኛው የእግዚአብሄር ዘር ሲዘራ እውነተኛው ምርት ያፈራል፣ ያም ክርስቲያን ነው። ያም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው።እውነተኛው

አዲስ ኪዳን ትምህርት በተዘራበት ቦታ እውነተኛው ቤተክርስቲያን ይኖራል፡፡

አምላክ ምንጊዜም ለህዝቡ እንዲከተሉት አብነት ይሰጣል፡፡ለኖህ መርከቢቱን እንዲሰራ ንድፍ ሰጠው (ዘፍጥረት 6)፡፡ ለሙሴ የማደርያውን ዲንኳን ከማስጠንቀቂያ ጋር ሰጠው፡፡ "እነሱም ለሙሴ ዲንኳኒቷን ሊሠራ ስለ ተረዳ ለሰማያዊ ነገር ምሳሌና ጥላ የሚሆነውን ያገለግላሉ በተራራው እንደተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበረና" (ዕብራዊያን 8፡5)፡፡ አሁንም በአዲስ ኪዳን እኛም ፊፁም የሆነውን አብነት ወይም ንድፍ የጌታ ቤተክርስቲያንን ሰጥቶናል፡፡ ኖህ እና ሙሴ ያንን የተሰጣቸውን ጠብቀው ተከትለውት እግዚአብሄርን እንዳስደሰቱት እኛም ስለ ቤተክርስቲያን የተሰጠንን ተከትለን የተጽፈውን እንደተጻፈው ብንፈጽም እግዚአብሄርን እናስደስተዋለን፡፡ ከዚያ ላይ ሳንጨምር ሳንቀንስ በሌላ ሳንተካ ማለት ነው (ዮሃንስ ራዕይ 22፡18~19)፡፡

የበተክርስቲያን ምንነትን በግልፅ ተምረናል ትክክለኛዋን በተክርስቲያን ልናውቅበት የምንችለውን ሁሉ አውቀናል ይህም ማን እንደመሰረታት፤ ዬት እንደተመሰረተች፤ መቼ እንደተመሰረተች፤ መጠሪያ ስሟ ማን እንዲሆነ፤ የአባላቶቿ መጠሪያ ምን እንዲሚባል፤ እንዴት እንደምናመልካት፤ ሥራዎቿ እንዴት እንደሆነ ወዘተ ነግሮናል፡፡ ራስ ማን እንደሆነ በምን ዋጋ እንደተገዛች ነግሮናል አዳኟ ማን እንደሆነ አውቀናል ስለዚህ ስለ እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ማንነት እና ምንነት አንዳችም ጥርጣሬ ሊኖረን አይችለም፡፡

ስለዚህ ማድረግ ያለብን መጽሃፍ ቅዱስን ማጥናት ማመን የሚልውን እውነት ስንከተል የእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን አባል እንሆናለን ምክንያቱም የሚበቅለው የተዘራው ነውና፡፡ ያንን የተከተለ ያመነ የታዘዘ ሁሉ የዚህች ቤተክርስቲያን አባል ይሆናል፡፡

የጌታ ቤተክርስቲያን በሁሉም ቦታ በዓለም ዙሪያ ይኖራል በዬትኛውም ጊዜ በዬትኛውም ቦታ ልትኖር የምትችል ናት ይህቺ ኤተክርስቲያን፡፡ዛሬ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እያደገች ዘሩን እየዘራች ትገኛለች ምክን ያቱም መጽሃፍ ቅዱስን ስለምትከተል ብቻ ነው፡፡ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን መከፋፈልን ታወግዛለች ክርስቶስንና ትምህርቱን ታከብራለጭ ይህ አሁን በመጽሃ ቅዱስ ውስጥ የምታነባት ቤተክርስቲያን ናጥ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት ድርጅት ስብስብ አይደለችም፡፡ ካቶሊክ አይደለችም፡፡ ፕሮተስታንት አይደለችም፡፡ ኦርቶዶክስ አይደለችም፡፡ አድቤንስት ሞርሞን ወዘተ አይደለችም፡፡ ታዲያ ምንድናት? በቀላሉ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናጥ በቃ፡፡

እጌታ ቤተክርስትያን በምድር ላይ ራስ ውይም ዋና መሥሪያ ቤት የላትም፡፡ ለማንም የጌታን ክብር አንሰጥም፡፡ በምድራዊ ጥበብ ምንም

አይነት ድርጅታዊ ነገር የለንም እያንዳንዱ ጉባኤ ራሱን የቻለ ነው። በማንም ላይ ጥገኛ አይደለም። የየራሳቸው ሽማግሌዎች አላቸው። የየራሳቸው አስተማሪዎች ሰባኪዎች ዲያቆናት አላቸው አባላት አላቸው።

የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሁሌም ጠላቶች ነበሯት ስለዚህም ዛሬም ጠላቶች አሏጥ የእነሱን ምሳሌ የማትከተል ቤተክርስቲያን ስለሆነች የሃይማኖት ድርጅት ይቃወሟታል። እነሱን ስለማንተባበራቸው እና ፍጥነታቸውን ስለማንቀበል ይናደዱብናል። መጽሃፍ ቅዱስን ብቻ የሚመክር ሰው እንዳለ ጠንቅቀው ይውቃሉ። የስውን ትምህርት የሚከተሉት ጊዜ የክርስቶስን እንደምንከተል ስሙን እንደምንለብስ ያውቃሉ። ሰውን ተከትልው የስውን ስም ሲለብሱ። በእኛ ላይ የያዙት መሣሪያ እውነት ሳይሆን የህዝቡን ልብ ለማድላት እኛን ለማሣሣት ወዘተ ነው። ድካማቸው ግን ከንቱ ነው/

የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በዘመናት ውስጥ አሸናፊ ናጥ የምድር ሁሉ ጠላቶች እና የዓለም ሁሉ ሠይጣናት ሊያስቆሟት አይችሉም። ምናልባት በአከባቢዋ ካሉት ስትወዳደር በቁጥር ጥቂት ልትሆን ትችላለጭ ነገር ግን ያቺ ጥቂቷ ወደ ህይወት መንገድ የምትወስድ ናት (ማቴዎስ 7፡13~14) ክርስቶስ አንዲት ቤተክርስቲያን አለው ለዚያች ቤተክርስቲያን ደግሞ ተመልሶ ይመጣል (ኤፌሶን 5፡27፣ ዮሃንስ 14፡1~6) እሱ የመንግስቱ ንጉስ ነው እናም ያቺን መንግስቱን ወደ እግዚአብሄር ሊወስዳት ይመጣል። ( 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡24) አንዲት ሙሽራ አለቸሁ እናም አንድ ቀን ያቺን ሙሽራ ሊወስድ ይመጣል (ዮሃንስ ራዕይ 21፡ 9) ያቺ ስሙን የለበሰቸውን ሊወስድ ይመጣል። ሌሎቹስ እንዴት ናቸው? ስለነሱ ክርስቶስ ተናግሯል። አላወቅኳቸሁም እላቸዋለሁ። አብ ያልተከለው ሁሉ ይነቀላል (ማቴዎስ 15፡13) ተሰብስበው ወደ እሳት ይጣላሉ።

የእኛ የዛሬው ምኞታችን ሰዎች ወደ ንፁህ የአዲስ ኪዳን ትምህርት እንዲመለሱ ነው። መጽሃፍ ቅዱስን ብቸኛው መመሪያቸው እንዲያደርጉት ነው። መጽሃፍ ቅዱስን እወቁ ከዚያ እውነትን ታውቃላቸሁ። እሱ የሚናገረውን አድርጉ ከዚያ ትድናላቸው። ከዚያም ከመጽሃፍ ቅዱስ ወዳንበባቸውት ቤተክርስቲያን ትጨመራላቸው።
የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ካልሆንክ። አባል እንድትሆን እናበረታታሃለን። በግዚአብሄር እመን።ንሠሃ ግባ። ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክር። እናም ተጠመቅ ከዝያ ትድናለሕ (ማርቆስ 16፡16፣ ሮሜ 10፡10፣ ሓዋርያት ሥራ 2፡38)። ከዚያ ጌታ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሃል አንተም ክርስቲያን ትሆናለህ (የሓዋርያት ሥራ 2፡47፣ የሓዋሪያት ሥራ 11፡26) ያንን ታደርጋለህ? እንድታደርግ ማንም አያስገድድህም። ነገር ግን መጽሃፍ ቅዱስህን የምታጠና ከሆነ

ክርስቲያን ብቻ መሆን እንደምትፈልግ እናምናለን እናም ቀሪ ህይወትህ ለጌታ ለመኖር በመሞከር እና ድንበር ለማስፋት የመንግስቱ አካል ትሆናለህ ።

## ጥያቄዎች
## ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ቤተክርስቲያን መቼ ተመሰረተች?
2. ይህቺ ቤተክርስቲያን አሁን አለች?
3. የጌታ ቤተክርስቲያን መሆኗን ለማረጋገጥ ባለፉት መቶ ዘመናት ቤተክርስቲያን መፈለግ መቻል አለበት?
4. ጌታ ቤተክርስቲያኑን ለምን ያህል ጊዜ ትቆማለች አለ?
5. የመንግስቱ ዘር ምንድነው?
6. ይህ ዘር ሲዘራ ምን ያመርታል?
7. እግዚአብሄር ለኖህ እና ለሙሴ የሰጠውን ተናገር
8. የጌታ ቤተክርስቲያን አብነት ወይም ንድፍ ዬት ነው የሚገኘው?
9. የጌታ ቤተክርስቲያን ምንነት መግለጫ ዬት ይገኛል?
10. ጌታ ስለ ቤተክርስቲያን ምን ነግሮናል?
11. እውነተኛ የመጽሃፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን እንዴት ማወቅ እንችላለን?
12. ዛሬ የጌታ ቤተክርስቲያን ዬት ትገኛለች?
13. ቤተክርስቲያን የሃማኖት ድርጅት ናት?
14. የምድራዊ ራስ ወይም ዋና መስሪያ ቤት አላት?
15. የቤተክርስቲያን ጠላቶች እነማን ናቸው?
16. መሣሪያቸው ምንድነው?
17. ቤተክርስቲያን በዘመናት ሁሉ አሸናፊ ነበረች?
18. ክርስቶስ ለምን ተመልሶ ይመጣል?
19. ምኞታችን ምንድነው?
20. እስቲ ክርስቲያን ለመሆን እና የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ቅደም ተከተሉን ግለፅ_______

እውነት ወይም ሃሰት ብለህ መልስ

1. ክርስቶስ የመሰረታት ቤተክርስቲያን ዛሬም አለች
2. ክርስቶስ ያለው አንዷት ቤተክርስቲያን ብቻ ናት
3. የሱን ስም ለብሳለች
4. አንድ ሰው ለመዳን አባሏ መሆን አለበት
5. ክርስቶስ አንድ ቀን ለቤተክርስቲያኑ ተመልሶ ይመጣል።